# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የመንግሥት ኘሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ
# የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


ክፍል አንድ ..... 1

ማጠቃለያ/summary/ ..... 1

- መግቢያ ..... 8
  - የመንግሥት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አስፈጻሚዎች ተግባርና ኃላፊነት ..... 9
  - የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የመንግስት ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ያለው አደረጃጀት ..... 9
  - በመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ..... 10
  - የመንግስት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ምንጭ ..... 10
  - የኦዲቱ አላማ ..... 11
  - የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና ጭብጦች ..... 11
- የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative criteria/ ..... 13
- የአሰራር ሂደት (process description) መግለጫ ..... 15

ክፍል ሁለት ..... 16

- ግኝቶችና የመደምደሚያ ሀሳቦች ..... 16
  - የፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ክትትል መመሪያ በበርካታ በፕሮጀክት አስፈጻሚዎች ተግባራዊ ስላለመደረጉና ተገቢው ስልጠና ስላለመሠጠቱ፣ ..... 16
  - በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች የትግበራ ስራ ከመጀመራቸው በፊት  የቅድመ ትግበራ ግምገማ (appraisal) የማይደረግላቸው ስለመሆኑ፣ ..... 18
  - በቅድመ ትግበራ ግምገማ የተሰጡ የማሻሻያ ነጥቦች  በፕሮጀክት ሰነድ ላይ የተካተቱ መሆናቸው የማይረጋገጥ ስለመሆኑ ..... 21
  - በቅድመ ትግበራ ግምገማ አስተያየት የተሰጠባቸው የፕሮጀክት ሰነዶች ተስተካክለው የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ ስላለመኖሩ፣ ..... 23
  - በፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶች የባለድርሻ አካላት (stakeholders) ሚና የማይገለጽ እና ተገቢው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ስለመደረጉ የማይረጋገጥ ስለመሆኑ፣ ..... 24
  - የልማት ፕሮጀክቶች ደረጃ የሚሰጣቸው በሚመደበው ገንዘብ መጠን ብቻ ስለመሆኑ፣ ..... 25
  - ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ጥናት ያልተዘጋጀላቸው የልማት ኘሮጀክቶች ስለመገኘታቸው፣ ..... 26
  - የልማት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እና የገንዘብ መጠን የማይጠናቀቁ ስለመሆኑ፣ ..... 28
  - ኘሮጀክቱ አዋጪ መሆን/አለመሆኑ ጥናቱ ተጀምሮ ከፍተኛ ወጪ ከተደረገበት በኋላ የተቋረጠ ኘሮጀክት ስለመኖሩ 33
  - የፕሮጀክቶችን ሥራ በሚከታተሉት ሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች መካከል ተገቢው ቅንጅታዊ አሰራር ስላለመኖሩ፣ ..... 34
  - ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርበው የሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የሚቀርብ ስላለመሆኑ፣ ..... 35
  - ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርበው የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት ይዘት ወጥነት የሌለውና በፕሮጀክት ክትትል መመሪያው መሰረት  ስላለመሆኑ፣ ..... 36

የፕሮጀክቶች አተገባበር ሂደትን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የሚከናወነው የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የተቋረጠ ስለመሆኑ፣ ..... 38
በክትትል እና ግምገማ ወቅት የታዩ እና መስተካከል የሚገባቸው ስራዎች በፕሮጀክት አስፈጻሚው አካል በትክክል ስመስተካከሉ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ስላለመኖሩ፣ ..... 39
ከአስፈጻሚዎች የሚቀርበው የአፈጻጸም ሪፖርት የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የፋይናንስ እና የፊዚካል ክንውን የሚያካትት ስላለመሆኑ ..... 40
በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚዘጋጀው መረጃ ተመሳሳይ ስላለመሆኑ ..... 40
ለፕሮጀክቶች ከመነሻ ጥናት ጀምሮ እስከ ፍጻሜና ድኅረ ትግበራ ያለውን መረጃ ለማጠናቀርና ለመጠበቅ የሚያስችል የተዘረጋ ና ተግባራዊ የሆነ ስርዓት ስላለመኖሩ ..... 44
ለልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በየደረጃው የሚለቀቀው ተጨማሪ ገንዘብ ቀደም ብሎ የተፈቀደው በትክክል በሥራ ላይ መዋሉ ሳይረጋገጥ ስለመሆኑ፣ ..... 46
ሥራቸው ስተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የድህረ ትግበራ ግምገማ የማይከናወን ስለመሆኑ፣ ..... 47
ክፍል ሶስት ..... 49
የማሻሻያ ሃሳቦች ..... 49
አባሪ ..... 54
የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ..... 54

# ክፍል አንድ

## ማጠቃለያ/summary/

1. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በፌዴራል መንግስት አወቃቀር መሰረት ሁሉም በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ አካላት በፕሮጀክት ዝግጅት፣ ቅድመ ትግበራ ግምገማ፣ ትግበራ፣ ቁጥጥርና ክትትል እንዲሁም ድህረ ትግበራ ግምገማ ያላቸውን ኃላፊነትና ተግባር ለመወጣት የሚያስችል አደረጃጀት ያላቸው መሆኑን፣ የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዑደት በአስፈጻሚ መ/ቤቶች በትክክል እየተተገበረ መሆኑን፤ ከፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የሚፈለገው ውጤት (ስኬት) የተገኘ መሆኑን፤ የተመደበላቸው በጀት እና የሰው ኃይል የተጣለባቸውን ኃላፊነትና ተግባር በብቃትና በስኬታማነት ለመወጣት የሚያስችላቸው መሆኑን፣ የተመደበው ሃብት በአግባቡ በስራ ላይ እየዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲሁም ለፕሮጀክት አፈጻጸም ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱን እና በአፈጻጸም የሚታዩ ችግሮችን በመለየት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡
2. ይህን የኦዲት ዓላማ ለማከናወን በአንድ የኦዲት ጭብጥ (ትኩረት አቅጣጫ) እና አምስት ንዑስ የኦዲት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡
3. የኦዲት ጭብጡም የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለው ሥርዐት የሚዘጋጁ፣ ተገቢው ቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚከናወንባቸው፣ የሥራ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት የተዘረጋላቸው እና የርክክብና የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወንባቸው መሆናቸውን ማጣራት፣ የሚሉ ናቸው፡፡
4. እነዚህን የኦዲት ጭብጦች ለማጣራት 38 የኦዲት መስፈርቶች ተዘጋጅተው ጉዳዩ ለሚመለከተው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ቀርቦ፣ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡
5. በኦዲት ወቅት ከተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ውስጥ የልማት ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነድ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሳይከናወንባቸው በጀት የሚፈቀድላቸው መሆኑን፣ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሚከናወነው የክትትል እና ግምገማ ሥራ አናሳ መሆኑ፤ የአዋጭነት እና የዲዛይን ጥናት ሳይዘጋጅላቸው ወደ ትግበራ የገቡ ፕሮጀክቶች መኖራቸው፤ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ከታቀደላቸው ጊዜ እና የገንዘብ መጠን በላይ የሚፈጁ መሆኑ እንዲሁም በአስፈጻሚ

አካላት የሚዘጋጁ እና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሚቀርቡ የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርቶች የፕሮጀክቶችን አጠቃላይ የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም የማያሳዩ መሆኑ የሚሉ ናቸው፡፡

6. የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያ (guideline) በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የተዘጋጀ ቢሆንም በኦዲቱ በናሙና ከታዩ በውሃ ሃብት ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም በአንዳንድ በውጭ እርዳታና ድጋፍ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ይህንን መመሪያ በፕሮጀክት ዝግጅት እና አፈጻጸም ያልተጠቀሙበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

7. ለናሙና በኦዲት ከታዩ ኘሮጀክቶች፣ ከመንገድ ሴክተር 8፣ ከትምህርት ሴክተር 2፣ ከጤና ሴክተር 2፤ ከግብርና ሴክተር 2፤ ከውሃ ሴክተር 2 ፕሮጀክቶች እንዲሁም በውጭ እርዳታና ብድር ድጋፍ የሚከናወኑ የልማት ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነድ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የቅድመ ትግበራ ግምገማ ያልተከናወነባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

8. በቀረበው የቅድመ ትግበራ ግምገማ ውጤት መሠረት የተሰጡ የማሻሻያ ነጥቦችን በጥናት ሰነዱ ውስጥ አስፈጻሚዎች ማካተታቸውን /ማሟላታቸውን/ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬቱ የማይረጋገጥ ሲሆን፤ አስፈጻሚዎችም የጥናት ሰነዱን በስንት ጊዜ አስተካክለውና አሟልተው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ማቅረብ እንዳለባቸው የተገለጸ እና ተግባራዊ የሆነ አሰራር የሌለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የቅድመ ትግበራ ግምገማ የተከናወነባቸውን የፕሮጀክት ሰነዶች ወደ ትግበራ ከገቡ በኋላ ለሚጨመሩ እና ለሚቀነሱ የሥራ መጠኖች በድጋሚ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ለግምገማ ቀርበው እንዲገመገሙ የሚደረግበት አሰራር የሌለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

9. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ከቀረቡ የፕሮጀክት የጥናት ሰነዶች የግምገማ ውጤት በሚሰጠው የማሻሻያ ነጥቦች ላይ ከኘሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተከናውኖ እና የስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ በፊርማ መረጋገጥና መቅረብ እንዳለበት የሚገልጽ አስተያየት የማይካተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ባለመደረጉ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት ከባለድርሻ አካላት ጋር አለመግባባት የሚፈጥርና እገዛቸውንም ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡ እንዲሁም የአካባቢ ግምገማ ተጽዕኖ ውጤት ጉዳዩ ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘቱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ የተጽእኖ ግምገማ አስፈላጊነትን ከታሰበው ዓላማ አያደርስም፡፡

10.የልማት ኘሮጀክቶች ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም አነስተኛ ለመሆናቸው የሚገለጹበት የደረጃ አሰጣጥ መስፈርቱ በሚመደበው የገንዘብ መጠን እንጂ፣ የፕሮጀክቶችን ባህሪ፣ የቴክኖሎጂ ውስብስብነት እና ሌሎች መመዘኛዎችን የማያካትት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የደረጃ አሰጣጥ በአስፈጻሚዎች ዘንድ የማይታወቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

11.ማንኛውም የግንባታ ፕሮጀክት ሥራ ከመጀመሩ በፊት የአዋጭነት ጥናት እና ዝርዝር ንድፍ ጥናት (ዲዛይን) ስራ ሊዘጋጅለት የሚገባ ቢሆንም በናሙና በኦዲት ከታዩት ፕሮጀክቶች ውስጥ ከመንገድ ሴክተር ለዱር ቤቱ - ሻሁራ፣ ሻሁራ -ጎለጎ መንገድ ስራ ፕሮጀክቶች የፊዚቢሊቲ እና የምህንድስና ዲዛይን ጥናት ያልነበራቸው ሲሆን፣የኮምቦልቻ-መካነሰላም መንገድ ስራ ፕሮጀክት ደግሞ የአዋጪነት (ፊዚቢሊቲ) ጥናት ያልነበረው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከጤና ሴክተር የሃይጅንና አከባቢ ጤና ትምህርትና ቁጥጥር እና የመድሀኒት አያያዝና አጠቃቀም ማጠናከርያ ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ለብቻው አልተዘጋጀለትም፡፡

12.በኦዲት በናሙና ከታዩ የመንገድ ሴክተር ፕሮጀክቶች ውስጥ በታቀደላቸው የጊዜ ገደብ ያልተጠናቀቁ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች ተገኝተዋል፡፡ ኦዲቱ እየተከናወነ ባለበት ወቅት በተገኘው መረጃ መሠረት ሶስት (3) የመንገድ ፕሮጀክቶች በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ይጠናቀቃለው ተብሎ በእቅድ የተያዙ ቢሆንም ሳይጠናቀቁ ቀርተው በመስከረም ወር 2003 ዓ.ም. የነበራቸው አፈጻጸም ከ 45% እስከ 79% ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የእንዳቶ -ጋሰራ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ለግንባታ መጀመሪያ ከተያዘለት የኮንትራት ውል ብር 390,343,766.96 ዋጋ ለውጥ ተደርጎ ወደ ብር 715,153,664.83 ከፍ ተደርጎ መጀመሪያ ከተያዘለት የኮንትራት ዋጋ 83% ያህል ጭማሬ ያሳየ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

13.እንዲሁም ከውሃ ሃብት ልማት ሴክተር የከሰም ተንዳሆ የግድብና መስኖ ልማት ግንባታ ፕሮጀክት እንደ እ.ኤ.አ. በ2004 የተጀመረ ሲሆን በወቅቱ 1.7 ቢሊዮን ብር ይፈጃል ተብሎ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም እስከ 2002 በጀት ዓመት ብቻ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል፡፡ በዚህ ወጪም ቢሆን ሥራው ያልተጠናቀቀና በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ የነበረውን የፊዚካል አፈጻጸም ምን ያህል እንደሆነ በውሃ ሃብት ሚኒስቴር ከቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ ያልተገለጸ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

14.በትምህርት እና በግብርና ሴክተር ፕሮጀክቶቹን ዘግይቶ መጀመርና ዘግይቶ መፈጸም ችግር ያለ ሲሆን ለዚህም ምክንያቶች የአንዳንድ አጋሮች የማስፈጸሚያ ስልት ጥብቅ

መሆኑ፣ ከተግባሪዎች በወቅቱ ሪፖርት አለማግኘትና የባለሙያዎች መለዋወጥ፣ በግዢ ስርዓት መጓተት፣ መረጃዎች በሚፈለገው ፍጥነት ከተግባሪዎች ስለማይሰጡ በየጊዜው ማስተካከያ ለመስጠት ማስቸገሩ፣ በአጋርነት ከሚሰሩት ክልሎች የገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርት በወቅቱ ስለማይላክ፣ አበዳሪ ድርጅቶች ገንዘብ በወቅቱ የማይለቀቅ መሆኑ በምክንያትነት የተጠቀሱ ናቸው፡፡

15.በግብርና ሴክተር ስር ያለው የእንስሳት ሃብት ልማት ማስተር ፕሮጀክት የፋይናንስ ምንጩ ከእርዳታ የሆነ የፕሮጀክት ዝግጅቱ ሁለተኛ ደረጃ (ፌዝ) ደርሶ ተቋርጧል፡፡ በፕሮጀክት የመጀመሪያ ደረጃ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሳይደረግ ለፕሮጀክቱ ጥናት ዝግጅት በድምሩ 4,957,330.00 ብር ወጪ ተደርጎ እንዲቋረጥ መደረጉ የወጣውን ወጪ እና ጊዜ እንዲባክን ከመደረጉም በላይ ሐገሪቱ ለ20 ዓመታት የምትመራበትን ማስተር ፕላን አለመዘጋጀቱ ከኘላኑ ተግባራዊነት የሚገኘውን ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚያሳጣ በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

16.በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት እና የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መካከል ቅድመ ትግበራ ግምገማን በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይኸውም ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ሥራ የቀረቡ የልማት ፕሮጀክቶችን የጥናት ሰነዶች የግምገማ ሥራ ለመጠናቀቁ የጽሁፍ ማስረጃ ለበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሳይቀርብ ለፕሮጀክቶች በጀት የሚፈቀድበት አሰራር መኖሩ እንዲሁም ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ያልቀረቡ የልማት ፕሮጀክቶች በበጀት የታቀፉበት አሰራር መኖሩ ታውቋል፡፡

17.የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚመጣውን የፕሮጀክቶች የሩብ ዓመት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም የግምገማ እና የተጠቃለለ ሪፖርትና የግምገማ ውጤት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የማያቀርብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

18.ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት በማቅረብ በኩል የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ጥሩ የሚባል ልምድ ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርቶች እንደተገነዘብነው የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ አመት ብቻ ሳይሆን በየወሩ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያቀርባል፡፡

19.ከጤና ሴክተር አስፈጻሚ፣ ከትምህርት ሴክተር አስፈጻሚ እና ከግብርና ሴክተር ሐሮማያ ዩኒቨርስቲ አስፈጻሚዎች ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተለያየ ጊዜ የሚቀርበው የፕሮጀክት የፊዚካል

እና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርቶች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር በተዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ (ፎርማት) መሰረት እንዳልሆነ እና እንዲሁም የፋይናንሻል እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ አመቱ የማያቀርቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት አስፈፃሚ አካላት ለጉዳዩ ትኩረት ባለመስጠታቸው እንደሆነ ተገልጿል፡፡

20. የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶችን፣ የትምህርት ሴክተር ፕሮጀክቶችን፣ የግብርና ሴክተር ፕሮጀክቶችን እና የጤና ሴክተር ፕሮጀክቶችን የገ/ኢ/ል/ሚ/ር መ/ቤት ከፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የክትትል ሥራ እና የማጠናቀቂያ ግምገማ የማያከናውን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

21. የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ከባለድርሻ አካላት ጋር ክትትል እና ግምገማ ሥራን በቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ላይ እንደሚሳተፍ ይኸውም በቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት እስቲሪንግ ኮሚቴ (steering committee) ውስጥ የፊዚካል እና የፋይናንስ አፈጻጸም ጉዳይን በሚገመግመው የገ/ኢ/ል/ሚ/ር እንደባለድርሻ የሚሳተፍ መሆኑን የተገነዘብን ሲሆን ይህም ተሳትፎ እንደባለድርሻ አካል ሚናውን እየተወጣ መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

22. ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በሚቀርበው የፋይናንስ አፈፃፀም ሪፖርት አጠቃላይ የፋይናንስ ክንውን (ወጪ) የማያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም ከውሃ ሴክተር አስፈጻሚ፣ ከትምህርት ሴክተር አስፈጻሚ፣ ከጤና ሴክተር አስፈጻሚ እና ከግብርና ሴክተር አስፈጻሚ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በሚቀርበው የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ የፊዚካል እና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ጀምሮ ያለውን አጠቃላይ የፊዚካል እና የፋይናንሻል ክንውን የማያመለክት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

23. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መካከል በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች የኮንትራት ዋጋ ለእያንዳንዱ ከ 18 ሚሊዮን እስከ 496 ሚሊዮን ልዩነት ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

24. ስለኘሮጀክት አፈጻጸም ዑደትን በአስፈፃሚዎች የመረጃ ስርዓት መያዝን አስመልክቶ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ለእንዳቶ-ጋሰራ መንገድ ሥራ ኘሮጀክት የመጀመሪያ የዲዛይን ጥናት፣ የእንዳስላሴ-ደጀና-ዳንሻ እና ኮምቦልቻ-መካነሰላም መንገድ ሥራ ኘሮጀክት የዲዛይን ጥናት ለኦዲት ሊቀርብ ያልተቻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

25.በገ/ኢ/ል/ሚ/ር ትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ለኦዲት በናሙና የታዩና 8 የመንገድ ኘሮጀክቶችን እና ከውሃ ልማት ሴክተር 3 ኘሮዠቶች ኘሮጀክቱ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ጥቅምት 30/2003 ዓ.ም. ለኘሮጀክቶቹ የተፈጸመ አጠቃላይ ክፍያን የሚያሳይ መረጃ በትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ሊቀርብ አልቻለም፡፡

26.የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ከኘሮጀክት አስፈጻሚ አከላት በየደረጃው እንዲለቀቅላቸው ለሚጠይቁት ገንዘብ በቅድሚያ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት /የፋይናንስና የፊዚካል/ ሳይቀርብለትና ሳይገመገም ክፍያ የሚፈጸም ሆኖ ተገኝቷል፡፡

27.ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ አስተዋጽኦ ባላቸው ትላልቅ ኘሮጀክቶች የድህረ ትግበራ ግምገማ ማካሄድ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ቢታወቅም በኦዲቱ ወቅት ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከውሃ ሀብት ሚኒስቴር፣ ከሃሮማያ ዩኒቨርስቲ የግብርና ሚኒስቴር በተጠናቀቁ እና አገልግሎት መስጠት በጀመሩ ኘሮጀክቶች የድህረ ትግበራ ግምገማ የማይከናወን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

28.ስለሆነም፣ በገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር መ/ቤትና በአስፈፃሚ አካላት በመንግሥት ኘሮጀክቶች አፈጻጸም ከላይ በተመላከቱት ግኝቶች ላይ የሚከተሉት የማሻሻያ ሀሳቦች ተሠጥተዋል፡፡

- አስፈፃሚ አካላት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀውን የኘሮጀክት አዘገጃጀት፣ ቅድመ ትግበራ ግምገማ፣ ክትትል እና ግምገማ መመሪያን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት የገንዘብና ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ ማስተላለፍና ተግባራዊነቱንም መከታተል ይኖርበታል፡፡
- የቅድመ ትግበራ ግምገማ ማከናወን ያስፈለገበትን አላማ ከግብ ለማድረስ እና ሚ/ር መሥሪያ ቤቱ የሰጠውን ኃላፊነት በትክክል ለመወጣት እንዲያስችለው በቅድመ ትግበራ ግምገማ ወቅት የተሰጡ የማሻሻያ ነጥቦች በሙሉ በተባለው መሠረት መካተታቸው እና መስተካከላቸው የማረጋገጥበት ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
- በእያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ኘሮጀክት ላይ ተሣታፊ የሚሆኑ ባለድርሻ አካላት (Stakeholders) በዝርዝር ተለይተውና ኃላፊነታቸው ተገልጾ ለቅድመ ትግበራ በሚቀርበው የኘሮጀክት ጥናት ሰነድ ላይ መካተቱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (Environmental impact assessment) ጥናት የሚያስፈልጋቸው የኘሮጀክት አይነቶችም ተለይተው እንዲታወቁና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ውጤትም በሚመለከተው አካል ፀድቆ መቅረቡ መረጋገጥ አለበት፡፡

- የልማት ፕሮጀክቶችን ደረጃ ለመለየትና በፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ጉዳዮች ለምሣሌ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የመሣሠሉትን ለመወሰን እንዲያስችል በፕሮጀክቶች ደረጃ አሠጣጥ ላይ ከገንዘብ መጠን በተጨማሪ የፕሮጀክቱ ባህሪ፣ የቴክኖሎጂ ውስብስብነት እና ሌሎች መሥፈርቶች የሚካተቱበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
- ለማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ወደ ግንባታ/ትግበራ እንዲገባ የሚያስችለው የመንግሥት በጀት ከመፈቀዱ በፊት የአዋጭነት ጥናት እንዲሁም እንደ ፕሮጀክቱ አይነት እየተለየ የዝርዝር ንድፍ (Design) መቅረቡ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፡፡
- የመንግሥት የልማት ፕሮጀክት አስፈፃሚዎች አጥንተው ባቀረቡት እና በፀደቀላቸው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ገንዘብ መጠንና የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራቸው እንዲጠናቀቅ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለተፈፃሚነቱም መመሪያ ሊዘጋጅ ለተጨማሪው ጊዜና ገንዘብ ገደብ (Maximum limit) ሊወሰንለት ይገባል፡፡
- የልማት ፕሮጀክቶች አስፈፃሚዎች በቅድመ ትግበራ ግምገማ ወቅት የተሰጣቸውን አስተያየት ተፈፃሚ እንዲያደርጉ፣ የፕሮጀክት ዑደትን ጠብቀው ሥራቸውን እንዲያከናውኑና ብቃት ያለው የፕሮጀክት አስተዳደር ሥርዓት እንዲሠፍን ለማድረግ፣ እንደሁም ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በተሟላ መልኩ እንዲቀርብና የተጠያቂነት መርሕ ተግባራዊ እንዲሆን ለማስቻል በልማት ዕቅድና ጥናት እና በበጀት ዝግጅትና አስተዳደር የሥራ ዘርፎች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር እንዲሰፍን መደረግ አለበት፡፡
- እያንዳንዱ የፕሮጀክት አስፈፃሚ መ/ቤት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያቀርበው የአፈፃፀም ሪፖርት ወጥነት ያለው፣ አጠቃላይ የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀሙን የሚያመላክት፣ የታቀደ እና የተከናወነውን በንፅፅር የሚያሣይ እንዲሆን መመሪያ ሊተላለፍና ተፈፃሚ እንዲሆን ጥረት መደረግ አለት፡፡
- ለእያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት የተለዩትና የሥራ ድርሻቸው በዝርዝር እንዲታወቅ ከተደረገው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በፕሮጀክቱ የክትትልና ግምገማ ሥራ ላይ ተሣታፊ የሚሆኑበት ሥርዓት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- እያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት ከመነሻ ጥናት ጀምሮ የፕሮጀክቱ ሥራ እስከ ተጠናቀቀበትና የትግበራ ሥራ እስከ ጀመረበት ጊዜ ያለውን ሂደት (የድህረ ግምገማን ጨምሮ) መረጃ እንዲዘጋጅለት ያስፈልጋል፡፡ መረጃዎቹም በአስፈፃሚ መ/ቤቶችና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ሊገኙና ተመሣሣይነት ያላቸው እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም እንዲሆን ተገቢው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡

# መግቢያ

29. የፌዴራል መንግስት የአገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ ና ዕቅድ ለማውጣትና ለማስፈፀም የሚያስችል ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 51 ተራ ቁጥር 2 ተሰጥቶ ል:: በዚሁ መሠረት የአጠቃላይ፣ የመድበለ ዘርፎች ና የክፍላተ ኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫዎችን የሚያመለክቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፀው ሥራ ላይ ንዲውሉ ተደርገዋል:: ከ ነዚህ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ዓላማዎች በተመነዘረ የተሟላ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ዘመን ዕይ ኢኮኖሚውን ለመምራት የሚያስችል አገራዊ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ የመጀመሪያው የአምስት ዓመት የልማት ዕቅድ (PASDEP) ከ**1998-2002** ዓ.ም ተዘጋጅቷል::

30. ይኸው ዕቅድ ከአገር ራዕይ የተመነዘረ ተቋማዊ ራዕይን ንደ አቅጣጫ የያዘና ተቋማዊ ተልዕኮን ለማስፈፀም ግልፅ ዓላማዎችና ግቦች ያሉት፣ በፌዴራል አደረጃጀትና ባልተማከለ የኢኮኖሚ አመራር ላይ የተመሰረተ አገራዊ የልማት ዕቅድ የረጅም ና የመካከለኛ የትግበራ የጊዜ ማዕቀፎች እንዲኖሩት ተደርጎ ከዕቅዱ ዘመን ጀምሮ በስራ ላይ እየዋለ ይገኛል:: በ ነዚህ ማዕቀፎች ላይ በመመሥረት የፌዴራልና የብሔራዊ ክልላዊ መንግስ ት በየራሳቸው ተጨባጭ ሁኔ ዎች ዓመ ዊ ዕቅድና በጀት አስተሳስረውና አዋህደው በማዘጋጀት ሥራ ላይ ያውላሉ::

31. የረጅምና መካከለኛ ዘመን ጠቋሚ የልማት ዕቅዶች ዝግጅትና የአፈፃፀም ግምገማ አገራዊ ይዘት ያላቸው ሲሆን የልማት ፕሮጀክቶች ጥናትና ግምገማ፣ የዓመ ዊ ዕቅድና በጀት ዝግጅት ሂደቶች የሚመለከቱት የፌዴራል መንግስቱን ነው:: የመንግስት ፕሮግራም በባህሪው በጊዜ ገደብ ያልተገደበ እቅድና ቀጣይነት ያለው የልማትና የኢንቨስትመንት ሥራዎች ሲሆኑ በስሩ የተወሰነ የጊዜ ገደብና ግብዓት ያላቸው የተወሰኑ ፕሮጀክቶችን ይይዛል::

32. በመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች አማካኝነት የሚካሄዱ የልማት ስራዎች በተለያዩ የፌዴራልና የብሄራዊ ክልላዊ መንግሥታት አስፈጻሚ አካላት የሚከናወኑ ሲሆኑ እነዚህ ስራዎች ከምልመላ፣ዝግጅትና ማጽደቅ እስከ ትግበራ እና ድህረ ትግበራ ግምገማ ባሉት የሥራ ሂደቶች ወጥነት፣ግልጽነት፣ተጠያቂነት እና ተፈጻሚነት ባለው ስርዓት እንዲያልፉ መደረግ አለባቸው::

## የመንግሥት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አስፈጻሚዎች ተግባርና ኃላፊነት

### 33.የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

- የልማት ፕሮጀክቶችን ዓመታዊ የማስፈጸሚያ በጀት ማጽደቅ (Ratification)፣
- የልማት ፕሮጀክቶችን የግማሽና ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶች በመመርመር ውሳኔ መስጠት፣

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት

- ከልማት ፕሮጀክቶች አሠራር ጋር የተያያዙ ደንቦችን ማውጣት፣
- የማስፈጸሚያ ካፒታል መጠናቸው ከ5ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የሆኑና በብድር በሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ድርድር እንዲካሄድ መፍቀድ፣ የብድር ስምምነት ሰነዶችን መርምሮ ማጽደቅ፣
- የአፈጻፀም ሪፖርቶች በመመርመር ውሳኔና መመሪያ መስጠት፣

### 34.የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

- የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች የአዘገጃጀትና የአፈጻጸም ስርዓት መዘርጋት፣
- ለፋይናንሲንግ በሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ላይ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ማካሄድ፣

### 35.የክፍላተ ኢኮኖሚ አስፈጻሚ መ/ቤቶች

- የልማት ፕሮጀክቶችን ክፍለ ኢኮኖሚያዊ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣
- የልማት ፕሮጀክቶችን መመልመል፣ማጥናትና ማዘጋጀት፣
- የልማት ፕሮጀክቶችን መተግበር፣ አፈጻጸማቸውን መቆጣጠር፣መከታተልና በየሶስት ወሩ(እንደ አስፈላጊነቱ ከዚያም ባነሰ ጊዜ) የአፈጻጸም ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ፣ የድህረ ትግበራ ግምገማ ማካሄድ፣

### 36.የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የመንግስት ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ያለው አደረጃጀት

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአጠቃላይ በሶስት ዘርፎች የተደራጀ ሲሆን እነሱም፡-

- የልማት እቅድና የኢኮኖሚ አስተዳደር ዘርፍ
- የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርና ቁጥጥር ዘርፍ
- የኢኮኖሚ ትብብር ዘርፍ

ናቸው፡፡

37.ከመንግስት ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በቀጥታ ጉዳዩ የሚመለከተው

38.የልማት እቅድና የኢኮኖሚ አስተዳደር ዘርፍ ሚ/ር ደኤታን ሲሆን በሥሩ ስድስት ዳይሬክቶሬቶች አሉት፡፡ እነሱም፤

39.የልማት ዕቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት፣ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲና ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት፣ የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት ዳይሬክቶሬት፣ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት፣ የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት ናቸው፡፡

40.የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶችን የቅድመ ትግበራ ግምገማ የማድረግ እና አተገባበሩን የመከታተል ኃላፊነት በዋናነት የተሰጠው ለልማት እቅድና ጥናት እና ለበጀት ዝግጅት ዳይሬክቶሬቶች ነው፡፡

<u>በመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሂደት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት</u>

41.የልማት ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት አጸዳደቅና አፈጻጸም ስርዓት ተፈጻሚ የሚሆንባቸው አደረጃጀቶች የመንግስት አስፈጻሚ አካላትን ተግባራትና ኃላፊነቶች መሰረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡በመሆኑም ሥርዓቱን ለማስፈጸም ተጨማሪ አደረጃጀት ሳያስፈልግ ለእያንዳንዱ አስፈጻሚ አካል በአዋጅ ከተሰጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች አኳያ ሥራ ላይ ያለውን አደረጃጀት መጠቀም ነው፡፡

<u>የመንግስት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ምንጭ</u>

42.በመንግስት የሚከናወኑ የተለያዩ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ምንጩ ከማዕከላዊ ግምጃ ቤት፤ከውጭ አገር ዕርዳታ እንዲሁም ከውጭ አገር ብድር የሚገኝ ነው፡፡ ከውጭ የሚገኘው የፋይናንስ ፍሰት ሂደትም በሶስት አቅጣጫ ወይም ክፍል (channel) የሚከፈሉ ሲሆን፡-

**ቻናል** 1፡ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር ወደ በጀት ሲስተም የሚገባ፣

**ቻናል** 2፡ ለክፍላተ ኢኮኖሚ አስፈጻሚ አካሎች በቀጥታ የሚሰጥ፣

**ቻናል** 3፡ ቀጥታ ለፕሮጀክቶች ሥራ ላይ የሚውል፣

ናቸው፡፡

43.ከፌዴራል መንግሥት የበጀት አዋጅ ካፒታል በጀት መሰረት ከ2000-2002 ዓ.ም. በፌዴራል መንግስት የሚከናወኑ የመንግሥት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ብዛት በአማካይ በየዓመቱ 569 ያህል ነው፡፡

| በጀት ዓመት | የተመደበ ካፒታል በጀት በብር |
|---|---|
| 1999 | 16,067,223,499.00 |
| 2000 | 18,890,014,657.00 |
| 2001 | 23,435,586,178.00 |
| 2002 | 29,110,957,210.00 |

## የኦዲቱ አላማ

44.የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዑደት በገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና በክፍላተ ኢኮኖሚ አስፈጻሚ መ/ቤቶች በትክክል እየተተገበረ መሆኑን፤ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ውጤታማ መሆኑን፤ ለልማት ፕሮጀክቶች የተመደበው ሃብት በአግባቡ በስራ ላይ እየዋለ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የፕሮጀክት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋቱንና ተፈጻሚ መደረጉን፣ እንዲሁም በአፈጻጸም የሚታዩ ችግሮችን በመለየት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው።

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና ጭብጦች

45.ክዋኔ ኦዲቱን ለማከናወን አንድ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Issue) እና አምስት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ተዘጋጅተው በማስቀመጥ ዝርዝር ክዋኔ ኦዲት ተከናውኗል። የኦዲት አቅጣጫዎቹም፣

1. የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለው ሥርዓት የሚዘጋጁ፣ ተገቢው ቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚከናወን፣የሥራ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት የተዘረጋ እና የርክክብና የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወን መሆኑን ማጣራት፣
   - 1.1. የመንግሥት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ ትግበራ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያ መሠረት ወጥነት ባለው አሠራር ተዘጋጅተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርቡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
   - 1.2. ለማናቸውም የመንግሥት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ ከመፈቀዱ በፊት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚከናወንባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣
   - 1.3. የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ በማከናወን ላይ በሚገኙ ማናቸውም የመንግሥት ፕሮጀክቶች ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲሁም አስፈፃሚ መ/ቤቶች የክትትልና

ግምገማ ሥራ ቋሚ በሆነ የጊዜ ሠሌዳ መሠረት የሚያከናውኑ መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.4. ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት በየደረጃው (Phases) ለሥራ ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ ከመፈቀዱ በፊት የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ተዘጋጅቶና ቀደምት ሥራዎች በትክክል ለመከናወናቸው የሚረጋገጥ መሆኑን ማረጋገጥ፣

1.5. የልማት ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እና ገንዘብ እንዲሁም በተገቢው መንገድ ለመጠናቀቃቸው የግምገማ ሥራ የሚከናወን፣ርክክብ የሚፈጸም እና ድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወን መሆኑን ማረጋገጥ፣የሚሉ ናቸው፡፡

# <u>የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች/Evaluative criteria/</u>

46.ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian performance audit standards) መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱን ለማከናወን 38 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ በቅድሚያ አስተያየት እንዲሰጥባቸው ጉዳዩ ለሚመለከተው የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የልማት እቅድና በጀት ዳይሬክቶሬት ቀርቦ አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## <u>የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ/ስልት/</u>

47.ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በመንግስት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዑደት ያለው ተግባር ላይ የተመረኮዘ ሲሆን አፈጻጸሙን ለማየት፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴርና በውሃና ኢነርጂ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤቶች ሥር የሚተዳደሩ፣ ከመንገድ 8፣ ከጤና 2፣ ከትምህርት 2 ከግብርና 3፣ ከውሃ 3፣ በድምሩ 18 ኘሮጀክቶች በናሙና ተመርጠው እንዲሁም የተለያዩ የኘሮጀክት አጋሮች ከኘሮጀክቶቹ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በኦዲቱ ታይተዋል፡፡ እነርሱም:-

### <u>ከመንገድ ልማት ሴክተር ስምንት ፕሮጀክቶች</u>

48.ለዱር ቤቴ-ሻሁራ፣ ሻሁራ-ጎለጎ ፣ እንዳ ስላሴ-ደደቢት፣ ደደቢት-አዲ - ረመጥ፣ አዲ - ረመጥ ደጀና-ዳንሻ፣ ግንደወይን-መካነሰላም፣ መካነሰላም-ኮምቦልቻ እና እንዳቶ-ጋሰራ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት

### <u>ከጤና ሴክተር ሁለት ፕሮጀክቶች</u>

49.ለመድሀኒት አያያዝና አጠቃቀም ማጠናከር እና የሃይጅንና አካባቢ ጤና ትምህርትና ቁጥጥር ፕሮጀክት

### <u>ከትምህርት ሴክተር ሁለት ፕሮጀክቶች</u>

50.ለሃሮማያ ዩኒቨርስቲ ማጠናከሪያ እና ድሬደዋ መለስተኛ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ማጠናከሪያ ፕሮጀክት

__ከግብርና ልማት ሴክተር ሶስት ፕሮጀክቶች__

51.የኢትዮጵያ ግብርና ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት፣ ቡና ተክል ማሻሻያ ፕሮጀክት እና እንስሳት ሃብት ልማት ማስተር ፕላን ፕሮጀክት

__ከውሃ ልማት ሴክተር ሶስት ፕሮጀክቶች__

52.የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን፣ የቆጋ የመስኖ ልማትና ተፋሰስ እንክብካቤ እና ከሰም ተንዳሆ ግድብ እና መስኖ እንክብካቤ ፕሮጀክት

ናቸው፡፡

53.የመረጃ አሰባሰብ ዘዴውም ከላይ ከተጠቀሱት የሴክተር መ/ቤቶች እንዲሁም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር ቃለ-ምልልስ በማድረግ እና የተለያዩ የሥራ ወረቀቶች በማሰባሰብና ክለሳ በማድረግ፣ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በመስክ ጉብኝትም የእንዳቶ -ጋሰራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት፣ የሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ማጠናከሪያ ፕሮጀክት፣ የድሬዳዋ ቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የሐረሪ ክልል ውኃና ፍሣሽ ባለሥልጣን ታይተዋል፡፡

## የአሰራር ሂደት (process description) መግለጫ

54.**የፕሮጀክት ምልመላ (Project Identification)**

ፕሮፋይል በተዘጋጀላቸው የፕሮጀክት ሀሳቦች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የማጣራት ስራ ተከናውኖ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የፕሮጀክት ሀሳቦች ወደዝግጅት ሂደት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

55. **ዝግጅት (Preparation)**

በፕሮጀክት ምልመላ ሂደት የሚመረጡና የአዘገጃጀት ቅደም ተከተል የሚወጣላቸው የፕሮጀክት አማራጭ ሀሳቦች በዝርዝር የሚጠኑበትና አዋጪ መሆንና አለመሆናቸው ይረጋገጣል፡፡

56. **ቅድመ ትግበራ ግምገማ (Appraisal)**

ቅድመ ትግበራ ግምገማ የአዋጪነት ጥናት ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በሚዘጋጅ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ሰነድ ላይ የክለሳ ስራ ይከናወናል፡፡ በዚህም ኘሮጀክቱ ወደትግበራ እንዲሸጋገር፣ እንደገና እንዲዘጋጅ ወይም ውድቅ እንዲሆን ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

57. **ድርድር፣መረጣና ማጽደቅ (Negotiation, Selection and Approval)**

**ድርድር፡-** በፕሮጀክቱ ባለቤት እና ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም የገንዘብ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ በሚያደርግ ተቋም አጋር መካከል ተፈጻሚ በሚደረጉ ግዴታዎች ዙሪያ የመግባቢያ ውይይት ይደረጋል፡፡

**መረጣ፡-** የቅድመ ትግበራ የግምገማ መመዘኛዎችን ከሚያሟሉ ፕሮጀክቶች መካከል የተወሰኑትን ወይም ሁሉም ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ ይወስናል፡፡

**ማጽደቅ፡-** በድርድር ሂደት የጋራ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውና ወደ ትግበራ እንዲሸጋገሩ የተመረጡ ፕሮጀክቶች በፊርማ ይፀድቃሉ፡፡

58. **ትግበራና ክትትል (Implementation & Monitoring)**

ወደ እንቅስቃሴ የገቡ ኘሮጀክቶች ላይ የክትትልና ግምገማ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

# ክፍል ሁለት

## ግኝቶችና የመደምደሚያ ሀሳቦች

**የፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ክትትል መመሪያ በበርካታ በፕሮጀክት አስፈጻሚዎች ተግባራዊ ስላለመደረጉና ተገቢው ስልጠና ስላለመሠጠቱ፣**

59.በፌዴራል ደረጃ ለሚገኙ የልማት ፕሮጀክት አስፈጻሚዎች ለፕሮጀክት ዝግጅት፣ቅድመ ትግበራ ግምገማ እና ክትትል ሥራ የሚረዱ መመሪያዎች (guidelines) በገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሊዘጋጁና ለሁሉም መ/ቤቶች ሊሠራጩ ይገባል፡፡ እንደዚሁም መመሪያዎቹ የመንግሥት የክፍላተ ኢኮኖሚ አካላትን ወጥ እና የተሟላ የፕሮጀክት ዝግጅት እንዲሁም የፕሮጀክት አፈጻጸሙን በተቀናጀ እና በትክክል ለመምራት የሚያስችሉ እንዲሁም አስፈጻሚ አካላቱ በራሳቸው የውስጥ አቅም ወይም በውጭ አማካሪ ወይም በሁለቱም ፕሮጀክት ሲያዘጋጁ ሊከተሉት የሚገባ ቴክኒካዊ የዝግጅት መመሪያ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱም በመመሪያዎች ላይ ተገቢውን ሥልጠና ሊሠጥ ይገባዋል፡፡ አስፈጻሚ አካላቱም መመሪያዎቹን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

60.በኦዲት ወቅት እንደተረዳነው ሚ/ር መ/ቤቱ መመሪያው በወጣበት እ.ኤ.አ በ2004፣ 2006 እና በ2008 ዓ.ም. ለሁሉም የፌዴራልና የክልል መንግስት መ/ቤቶችና በወቅቱ ለነበሩ 8ቱ ዩኒቨርስቲዎች መሰራጨቱን የሚኒስቴር መ/ቤቱ የልማት ጥናትና እቅድ ዳይሬክቶሬት የልማት ኘሮጀክቶች ቡድን መሪ ገልፀዋል፡፡ የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልጠናም በቅድመ ትግበራ ግምገማ መመሪያ /Appraisal Guide line/ ላይ ብቻ ከ30-40 ለሚሆኑ ከተለያዩ መ/ቤቶች ለተውጣጡ ባለሙያዎች የተሰጠ ቢሆንም፣ በፕሮጀክት ዝግጅት (preparation)፣ ግምገማና ክትትል /monitoring & Evaluation/ ላይ አለመሰጠቱ ታውቋል፡፡

61.እንደዚሁም የልማት ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶች በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተዘጋጀውና በተሠራጨው የፕሮጀክት አዘገጃጀት መመሪያ መሰረት የሚዘጋጁ ስለመሆኑ ለኦዲት በናሙና ከተመረጡ የልማት ፕሮጀክቶች መረዳት እንደተቻለው

62.የውሃ ሃብት ሚ/ር በ1987 ዓ.ም.(እ.ኤ.አ.) በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት እንጂ (በ 2004፣2006 እና 2008 እ.ኤ አ.) የተዘጋጀውን መመሪያ እንደማያውቁት የፕላኒንግ ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር ገልጸዋል፡፡

63.ሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ የማጠናከሪያ ፕሮጀክት ግንባታ የፕሮጀክት ጥናት የሚያከናውነው በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተዘጋጀው መሰረት እንዳልሆነና መመሪያውም እንዳልደረሳቸው በዩኒቨርሲቲው ፕላንና ፕሮግራም ምክትል ኦፊሰር ገልጸዋል፡፡

64.የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአለም አቀፍ ደረጃ ለመወዳደር በሚያስችል መልኩ ፕሮፖዛል የሚያዘጋጅ መሆኑን፣ ነገር ግን በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተዘጋጀው መመሪያ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል የሚያዘጋጁት በመንግስት በጀት ሙሉ በሙሉ ለሚሸፈነው ለግንባታ ሥራ ብቻ እንደሆነ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀብት ማሰባሰብ ዳይሬክቶሬት ተ/ዳይሬክተር በቃለ ምልልስ ገልጸዋል፡፡

65.ስለዚሁ ጉዳይ በውጭ እርዳታና ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን የጥናት ሰነድ ዝግጅትን በተመለከተ የሚ/ር መ/ቤቱ የመንግስታት ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቃለ ምልልስ ወቅት እንደገለጹት በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተዘጋጀው የፕሮጀክት ቀረጻ መመሪያ መሰረት ፕሮጀክቶች ስለመዘጋጀታቸው ማረጋገጥ እንደማይችሉ ለዚህም ምክንያቱ አንዳንድ ለጋሽ ሃገሮች የራሳቸው መመሪያ(ፎርማት) ያላቸው ስለሆነ በዛ እንዲዘጋጅ እንደሚፈልጉ፣ ነገር ግን ወጥ የሆነ (እስታንዳርድ) ፎርማት የማይጠይቁ ለጋሽ መንግስታት የሚኒስቴር መ/ቤቱን ፕሮጀክት አዘገጃጀት መመሪያን እንዲጠቀሙ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቀረቡት የኘሮጀክት ጥናት ሰነዶች ሲታዩ፣ ወጥነት እና የተሟላ ይዘት ያልነበራቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

66.ስለሆነም ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች ለመረዳት እንደሚቻለው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እ.ኤ.አ. በ2004 የተዘጋጀው የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች የጥናትና የአፈጻጸም መመሪያዎች በበርካታ አስፈጻሚ መ/ቤቶች ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች አንዳንድ አስፈጻሚ መ/ቤቶች መመሪያው ስለመኖሩ እንኳ አለማወቃቸውና ሥራ ላይ እንዲውል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ በመሆኑ ነው፡፡

67.በነዚህም ምክንያቶች የተነሣ በፕሮጀክት ዝግጅት፣ ግምገማ እና ክትትል ሥራ ሂደቶች ላይ የተለያዩ አስፈጻሚዎች በተለያየ መንገድ እንዲያከናውኑ እና ወጥነት የጎደለው አሠራር እንዲሰፍን ከማድረጉም በላይ ሁኔታው በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ላይ ችግር እንዲፈጠር፣ የፕሮጀክት ሰነድ ዝግጅት ወጥነት የሌለው እንዲሆን፣ የክትትል፣ ግምገማና ርክክብ ሥራ

ደረጃውን የጠበቀ እንዳይሆን፣ አላስፈላጊ ለሆነ ወጪ የሚዳርግና ተጠያቂትን ለማስፈን የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች የትግበራ ስራ ከመጀመራቸው በፊት የቅድመ ትግበራ ግምገማ (appraisal) የማይደረግላቸው ስለመሆኑ፣</u>**

68. በአስፈጻሚ አካላት የሚዘጋጁ ረቂቅ የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች (draft project proposal and design) ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ቀርበው የቅድመ ትግበራ ግምገማ (ምዘና) ሊከናወንላቸው ይገባል፡፡ በቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚደረስባቸው ውጤቶች ፕሮጀክቱ ወደ ትግበራ እንዲሸጋገር (ከመጠነኛ ማሻሻያዎች ጋር) ወይም እንደገና እንዲዘጋጅ ወይም ውድቅ እንዲሆን ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

69. ይሁን እንጂ፣ ይህንን ሁኔታ ለማጣራት በናሙና ተመርጠው የጥናት ሰነዳቸው የታዩ አስራ ስምንት የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች ሁሉም የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሳይከናወንባቸው ወደ ትግበራ የገቡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

70. እነዚህም፦ **ከመንገድ ሴክተር** ዱር ቤቴ -ሻሁራ፣ ሻሁራ- ጎለጎ፣ እንዳ ስላሴ -ደደቢት፣ ደደቢት- አዲ-ረመጥ፣ አዲ-ረመጥ-ደጀና -ዳንሻ፣ ግንደ ወይን -መካነሰላም፣ መካነሰላም-ኮምቦልቻ እና እንዳቶ- ጋሰራ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት፣ **ከጤና ሴክተር** የመድሀኒት አያያዝና አጠቃቀም ማጠናከር፣ የሃይጅንና አካባቢ ጤና ትምህርትና ቁጥጥር፣ **ከትምህርት ሴክተር** ለሃሮማያ ዩኒቨርስቲ ማጠናከሪያ እና ድሬደዋ መለስተኛ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ማጠናከሪያ፣ **ከግብርናና ገጠር ልማት ሴክተር** የኢትዮጵያ ግብርና ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት ፣ ቡና ተክል ማሻሻያ ፕሮጀክት እና እንስሳት ሃብት ልማት ማስተር ፕላን ፕሮጀክት፣ **ከውሃ ልማት ሴክተር** የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት፣ የቆጋ የመስኖ ልማትና ተፋሰስ እንክብካቤ ፕሮጀክት እና ከሰም ተንዳሆ ግድብ እና መስኖ እንክብካቤ ናቸው፡

71. እንደዚሁም በውጭ እርዳታና ድጋፍ በፌዴራል እና በክልል መንግስታት የሚከናወኑ የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አንዳንድ የመንግስታት ለጋሾች ሊሠራ ከሚፈልጉት የፕሮጀክት አዘገጃጀት ፎርማት መሰረት ዝግጅቱን የሚያሟሉ ከሆነ ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ቀርበው እንዲገመገሙ አይደረግም፡፡

72.የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሳይደረግባቸው ወደ ትግበራ ስለገቡትና በጀት ስለተፈቀደበት ምክንያት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ቃለ ምልልስ ተደርጓል። በሚኒስቴር መ/ቤቱ የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት ቡድን መሪ በቃለ ምልልስ በሰጡት መልስ የጥናት ሰነዶቹ ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ያልቀረቡበት ምክንያት የተቀናጀ የፕሮጀክት ዝግጅት ግምገማና የአጸዳደቅ ስርአት አለመዘርጋቱ፣ ለዚህም የህግ ማዕቀፍ አለመኖር እንደሆነ ገልጸዋል።

73.በተጨማሪም የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት መልስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን፣ የመሰረተ ጤና አገልግሎት፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት የመሳሰሉት ጉዳዮች ለሕብረተሰቡ የግድ መሟላት ያለባቸው በመሆናቸው የአዋጪነት ብቃት ማረጋገጫ ግምገማ ላያስፈልግ እንደሚችል፣ በፕሮግራም ደረጃ መንግስት የተቀበላቸው ከሆኑ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሂደት ማለፍ ሳይጠበቅባቸው በበጀት ተደግፈው ወደ ትግበራ ሊሸጋገሩ እንደሚችሉ፣ ይሁን እንጂ ፕሮጀክቱ በበጀት በሚደገፍበት ወቅት በቅድሚያ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጠቀሜታው ተመዛዝኖ መታየት እንዳለበት ገልጸዋል።

74. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ዝግጅት እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሥር የተለያዩ ሴክተሮችን ከሚከታተሉ ከፍተኛ የበጀት ባለሙያዎች ጋር በተደረገው ቃለ ምልልስ እንደተገነዘብነው የቅድመ ትግበራ ግምገማን በሚመለከት ወጥ የሆነ አሰራር እና ግንዛቤ እንደሌለ ነው።

75.በበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የትምህርት ሴክተር ከፍተኛ የበጀት ባለሙያ ስለ ትምህርት ሴክተር ፕሮጀክቶች ሲገልጹ ሁሉም ፕሮጀክቶች የተሟላ ጥናት ተደርጎባቸው ወጪያቸው እና የሚተገበሩበት ቀን በትክክል ታውቆ አቅምን ባገናዘበ መልኩና በዝርዝር እንደማይቀርቡ፣ ብዙ ጊዜ ሥራዎች እንዲሰሩ እንጂ ቴክኒካዊ ሥራዎች ጎልተው የወጡበት ሁኔታ እንደሌለ ስለሴክተሩ ያለውን ሁኔታ በቃለ ምልልስ ገልጸዋል።

76.ከግብርና ሴክተር በጀት ባለሙያ ስለሴክተሩ ፕሮጀክቶች በሰጡት መልስ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ስለአለመከናወኑ የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉ ጠቅሰዋል:: ለምሳሌም ሲጠቅሱ የኢትዮጵያ ግብርና ግብይት ማሻሻያ ፕሮጀክት በብድር የሚከናወን ስለሆነ ፕሮጀክቱ በፓርላማ እንደጸደቀ በውጭ ሃብት ትብብር ዘርፍ እንደተገመገመ ይህም

የሆነው የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት ለመገምገም የሰው ሃይል መሟላት ችግር እና የቅንጅት አለመኖር ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

77.ከጤና ሴክተር በጀት ከፍተኛ ባለሙያ ስለ ሴክተሩፕሮጀክቶች የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሁኔታ በቃለ ምልልስ ሲገልጹ የጤና ሴክተር ሥር ያሉ ሥራዎች በፕሮጀክት ደረጃ የሚታዩ እንዳልሆኑ እና ከጤና ሴክተር ልማት ፕሮግራም ሰነድ እየወጣ እንደሚወሰድ ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ የፕሮግራም ሰነዱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተገመገመ መሆኑን እና የፕሮግራም ሰነዱ በቅድሚያ ሲቀረጽ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባለሙያዎች የተሳተፉ ስለሆነ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በኩል የፕሮጀክት ግምገማ የማይደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

78.በሚ/ር መ/ቤቱ የበጀት ዝግጅት እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስለጉዳዩ በቃለ ምልልስ በሰጡን ማብራሪያ አብዛኛዎቹ ፕሮጀክቶች በsector development program የታቀፉ ና በመንግስት እቅድ የተያዙ ስለሆኑ፣ በፕሮግራሙ ከተያዙት ውስጥ ለበጀት ጥያቄ የሚቀርቡት በአስፈጻሚ መ/ቤት ደረጃ ተጣርተው እንደሚሆንና በፕሮግራም ሰነድ ውስጥ የተካተቱ ከሆነ ቅደም ተከተል እየተሰጣቸው (prioritize) እንደሚሰሩ፣ ነገር ግን ለነዚህ ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት የሚጠየቁበት ሁኔታ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

79.ከመንግስታት ትብብር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስም በውጭ እርዳታ እና ብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ላይ የሚደረገው የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሥራ በቴክኒክ ረገድ የፕሮጀክት ሥርዓት መከተሉን ማጣራት ሲሆን፣ በራሳቸው ፎርማት የሚከተሉ ሀገሮች ፕሮጀክት ከሆነ የቅድመ ትግበራ ሥራ የማይከናወን መሆኑን፣ ነገር ግን በለጋሹ አገር ፍላጎት (Defined) ባልሆነ ፎርማት ሲመጡ እንዲጣሩ ለልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት እንደሚላኩ ገልጸዋል፡፡፡

80. የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ደግሞ በለጋሾች (Donors) የሚሰጥ እርዳታ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን በልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት በኩል የቅድመ ትግበራ ግምገማ መከናወን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

81.ይሁን እንጂ የቅድመ ትግበራ ግምገማ አስፈላጊነትና ግዴታ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘጋጀው Appraisal Guidelines for Public sector projects-መመሪያ ላይ የተገለጸ ሆኖ ሳለ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ ከሥራ ኃላፊዎቹ የተሰጠው መልስም ምን አይነት ፕሮጀክቶች

የቅድመ ትግበራ ግምገማ እንደማያስፈልጋቸው በግልጽ ተለይተውና አሳማኝ ምክንያት ቀርቦላቸው በበላይ ሃላፊዎች እንዲታወቅ ባልተደረገበት ሁኔታ የቅድመ ትግበራ ሥራ አለመከናወኑ አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የቅድመ ትግበራ ግምገማ አለመከናወኑ ፈርጀ ብዙ ችግር የሚያስከትል መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡የቅድመ ትግበራ ግምገማ አለመከናወኑ የፕሮጀክት አሰራር መርህንና ተቀባይነት ያለው የአሠራር ሥርዓትን የሚቃረን፣ ወጥነት ያለው አሠራር እንዳይሰፍን የሚያደርግ፣ ለገንዘብ ብክነትና ለሥራ አለመስተካከል የሚዳርግ፣ የባለድርሻ አካላት ተገቢውን ሚና እንዳይጫወቱ እና ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ተጠናቀው ለአገልግሎት እንዳይውሉ እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል መታወቅ አለበት፡፡ የተሟላ የጥናት ሰነድ ያልተረጋገጠበት እና የሞያተኞች አስተያየት ያልተሰጠበትን ፕሮጀክት በበጀት እንዲደገፍ ማድረግ ለመንግስት ተገቢ አይደለም፡፡

82.የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች በቅድመ ትግበራ ሂደት እንዲያልፉ አለመደረጉ አገሪቷ ካላት ውስን ሀብት፣ ከማህበረሰቡ የልማት ጥያቄ፣ የአካባቢ ግምገማ ተጽእኖ፣ የህብረተሰብን ጥቅም ከማስቀደምና የሴቶችን እኩልነት ከማረጋገጥና የስራ ጫና ከመቀነስ፣ አንጻር ሳይታዩ ሊያልፉ ይችላሉ፡፡

83.ስለሆነም የፕሮጀክት ሰነድ የክፍላተ ኢኮኖሚ አላማን ከማስፈጸም አንጻር በአስፈጻሚዎች የሪቪው ስራ ለመከናወኑ በቅድመ ትግበራ ግምገማ መታየት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ፕሮጀክቱ ከአገራዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግቦችን ከማሳካት አንጻር ያለውን አስተዋጽኦ የቅድመ ትግበራ ግምገማ በማከናወን ለአገራዊ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ መለካት ያስችላል፡፡

<u>በቅድመ ትግበራ ግምገማ የተሰጡ የማሻሻያ ነጥቦች በፕሮጀክት ሰነድ ላይ የተካተቱ መሆናቸው የማይረጋገጥ ስለመሆኑ</u>

84.ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የሥራ ማከናወኛ በጀት ከመፈቀዱ በፊት፣ የግምገማ ሥራውን ከሚያከናውነው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ክፍል በግምገማ ወቅት በተሰጠ አስተያየት መሠረት የተስተካከለ ለመሆኑ በጽሁፍ የተደገፈ ማረጋገጫ (approval) እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

85.ይሁን እንጂ በቅድመ ትግበራ ግምገማ ቀርበው ለተፈቀደላቸው ፕሮጀክቶች ዲዛይንና ዝርዝር ስራዎች ላይ ለሚጨመሩና ለሚቀነሱ ጉዳዮች በድጋሚ ለዳይሬክቶሬቱ ቀርቦ እንዲፈቀድ (እንዲገመገም) የሚደረግበት አሰራር ተግባራዊ ያልተደረገ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

86.ለዚህም የሥራ ሂደት ከተፈቀደው ዲዛይን ወይም የሥራ መጠን በተጨማሪ ለሚካተቱ ወይም ለሚቀነሱ ሥራዎች በድጋሜ ለዳይሬክቶሬቱ ቀርበው መገምገም አለባቸው፡፡

87.በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት፣ አምስት የተለያዩ የቅድመ ትግበራ ግምገማ የተከናወነባቸው የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የተሰጡ ማሻሻያ ሃሳቦች የቅድመ ትግበራ ግምገማውን ባከናወነው የሥራ ክፍል መካተታቸው እንደገና ያልተረጋገጠ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

88.እነኚህም ፕሮጀክቶች

- በሃረማያ ዩኒቨርሲቲ የSericulture እና Bio-fuel ዲፓርትመንት ለማቋቋምና እንዲሁም የወተት ተዋጽኦ ቤተ-ሙከራ ተቋም በጪሮ ከተማ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ቅርንጫፍ ግቢ ለማቋቋም የተደረገ ጥናት፣
- የምርት ዘሮችን ከኢትዮጵያ ሴት ገበሬዎች ፍላጎት ጋር የማላመድ እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም አዳዲስ ዘዴዎች፣
- የመድሃኒት ቁጥጥር እና ጉዳቱን መከላከያ የጥናት ሰነድ፣
- በመንገድ ልማት ዘርፍ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት ረቂቅ ጥናት፣ እና
- በአ.አ. ከተማ ለሚኖሩ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ማህበረሰብ ተኮር የውሃ አቅርቦት እና የንጽህና አገልግሎት የማሻሻል ጥናት፣

ናቸው፡፡

89.ይህ አይነቱ አሰራር ለምን ተግባራዊ እንዳልተደረገ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፣ በግምገማው ወቅት የተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦች በፕሮጀክት ሰነዶች በትክክል የተካተቱ መሆኑ በዳይሬክቶሬቱ የማይረጋገጥ መሆኑን የገለጸ ቢሆንም፣ ለምን ለመካተቱ እንደማይረጋገጥ የሰጡት ምክንያት የለም፡፡

90.በመሠረቱ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ማከናወን ያስፈለገበት በርካታ ምክንያቶች ያሉት ሲሆን ከነኚህም መካከል የመንግስት የበጀት ሥርዓት በጥናት ላይ የተደገፈ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ለአገር ልማት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንዲሆን የሚያስችል፣ ደረጃውን የጠበቀ እና የተጠያቂነት ሥርዐት የሰፈነበት አሠራር እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡

91.በኦዲቱ ወቅትም ለመገንዘብ እንደተቻለው በግምገማ ወቅት የተሰጡ የማሻሻያ ኃሳቦች በተባለው መንገድ በትክክልና በተሟላ ሁኔታ በጥናትና ዲዛይን ሰነዶች የተካተቱ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ለችግሩ ዋና ምክንያት ነው፡፡ ለዚህም በሚ/ር መ/ቤቱ በሚገኙት ሁለት ዳይሬክቶሬቶች ማለትም የልማት እቅድና ጥናት እና የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር መካከል የግንኙነት ሥርዓት ባለመኖሩ የግምገማው ውጤት ሳይታወቅ በጀት የሚለቀቅ በመሆኑ በመ/ቤቱ የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱን ከማመልከቱም በላይ የሚከናወኑትን የቅድመ ትግበራ ግምገማዎችና ማስተካከያዎች ጥረት አስፈላጊነት ፋይዳ ቢስ ያደርገዋል፡፡

92.ስለሆነም ተገቢው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱና ሞያዊ አስተያየት የተሰጠበት የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ የማሻሻያ ሃሳቦችን አስተካክሎና በድጋሚ እንዲቀርብ አለማድረጉ ተቀባይነት ያለው አሰራር ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>በቅድመ ትግበራ ግምገማ አስተያየት የተሰጠባቸው የፕሮጀክት ሰነዶች ተስተካክለው የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ ስላለመኖሩ፣</u>

93.የቅድመ ትግበራ ግምገማ የተከናወነባቸውን የፕሮጀክት ጥናት ሠነዶችን አስፈፃሚ መ/ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ ነጥቦች መሰረት የፕሮጀክት ሰነዱን አሟልተው የሚያቀርቡበት ጊዜ ሊወሰንና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ፣ በኦዲቱ ወቅት አሠራሩ ለመኖሩ በተደረገው ማጣራት፣ የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት በቅድመ ትግበራ ግምገማ ታይተው የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጣቸውን ሰነዶች በስንት ጊዜ ውስጥ ማስተካከያውን አሟልተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ እንዳለባቸው የተገለጸ እና ተግባራዊ የተደረገ የጊዜ ገደብ የለም፡፡

95.ከልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት የልማት ፕሮጀክቶች ቡድን መሪ ጋር ከተደረገ ቃለምልልስ ለመረዳት እንደተቻለው በቅድመ ትግበራ ግምገማ በተሰጠው የማሻሻያ

አስተያየት መሰረት ማስተካከያውን መቼ ማቅረብ እንዳለባቸው የተቀመጠ የጊዜ ገደብ አለመኖሩን አረጋግጠዋል፡፡

96.ስለሆነም የጊዜ ገደቡ ባለመኖሩ ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ቀርበው እንዲሻሻሉ አስተያየት የተሰጠባቸው የፕሮጀክት ሰነዶች በተወሰነ የጊዜ ገደብ ተሟልተው እንዳይቀርቡ በእቅድ የመመራት ሥርዓት እንዳይኖርና ወደሚቀጥለው የትግበራ ሂደት በወቅቱ ለመሸጋገር እንዳይቻል አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ የፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ መጓተት ሊያስከትል ይችላል፡፡

<u>በፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶች የባለድርሻ አካላት (stakeholders) ሚና የማይገለጽ እና ተገቢው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ስለመደረጉ የማይረጋገጥ ስለመሆኑ፣</u>

97.በእያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ላይ በሚከናወነው የቅድመ ትግበራ ግምገማ ላይ የፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት ዝርዝር ኃላፊነት እና የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ በትክክል መካተታቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

98.ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ከታዩ አምስት ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ከቀረቡ የልማት ፕሮጀክቶች የግምገማ ውጤት መረዳት እንደተቻለው፣ የልማት ፕሮጀክቱ ባለቤት ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለው የሥራ ግንኙነት በዝርዝር ታውቆና የስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ እንዲፈረም አይደረግም፡፡ ለትላልቅ ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ቀርቦ ተቀባይነት ለማግኘቱም የሚረጋገጥበት አሰራር ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

99.ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የፕሮጀክቶች የክትትል እና ግምገማ ቡድን መሪ በቃለምልልስ እንደተገለጸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ትልቁ ችግር ከመብራት ሃይል ኮርፖሬሽን፣ ከቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ከመጠጥ ውሃ አገልግሎት ድርጅቶች ጋር የስራ ቅንጅት አለመኖር እንደሆነና ከአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ጋር በተያያዘም በፕሮጀክት ጥናት ሰነዱ መካተቱን እንጂ ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት እንዳለበት ያልተገለጸ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

100. ስለሆነም በቅድመ ትግበራ ግምገማ ወቅት የእያንዳንዱን ፕሮጀክት ባለድርሻ አካላት ሚና እና ኃላፊነት በዝርዝር ተዘጋጅቶና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበት

ተቀባይነት ለማግኘቱና ስምምነት ለመደረጉ የሚረጋገጥበት ሥርዓት አለመኖር በፕሮጀክቶች የሥራ ሂደትና ትግበራ ወቅት ብዙ ውጣ ውረዶችንና አለመግባባትን የሚፈጥር መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በፕሮጀክት የሥራ ሂደት ወቅት ከባለድርሻ አካላት ሊገኝ የሚችለውን ፈርጀ ብዙ እገዛ ከማስተጓጎሉም በላይ የባለቤትነት ሥሜት እንዳይኖር፣ በቅንጅት ባለመሠራቱም የስራ መጓተት እንዲፈጠርና ስኬታማ እንዳይሆን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም አላስፈላጊ ለሆነ ወጪ ከመዳረጉም በላይ፣ ተጠያቂነት ሲኖር በቀላሉ ለመለየት ያስቸግራል፡፡

101. የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ተቀባይነት የማግኘቱ ጉዳይም የዘላቂ ልማት ማረጋገጫ ሂደት መሆኑም መታወቅ ይኖርበታል፡፡ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ውጤት ጉዳዩ ለሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘት የሚረጋገጥበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ የተጽዕኖ ግምገማ አስፈላጊነትን ከታሰበው ዓላማ አያደርስም፡፡ አሠራሩም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ጥናት የተፈለገውን ይዘት እንዳያሟላና የግዴለሽነት አሰራር እንዲሰፍን አስተዋጽኦ በማድረግ በተፈጥሮ ሃብት እና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ አላስፈላጊ ጉዳት እንዲከሰትና ለብክለት እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡ በዚህም ምክንያት የማህበራዊና የምጣኔ ሀብት ጉዳቶችን በማስከተል ለሐገር ልማትና እድገት ችግር ፈጣሪ ይሆናል፡፡

<u>የልማት ፕሮጀክቶች ደረጃ የሚሰጣቸው በሚመደበው ገንዘብ መጠን ብቻ ስለመሆኑ፣</u>

102. ለልማት ኘሮጀክቶች በሚመደብላቸው የፋይናንስ መጠን፣ በባህሪያቸው፣ በውስብስብነታቸውና በመሳሰሉት ደረጃ ለመስጠት መሥፈርት ሊዘጋጅላቸውና የደረጃ አሠጣጡም በአስፈጻሚዎች ሊታወቅ ይገባል፡፡

103. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አሠራር ለልማት ፕሮጀክቶች ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን የፋይናንስ መጠን መሰረት በማድረግ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና አነስተኛ ተብለው ኘሮጀክቶች በልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት መስፈርት ተቀምጦላቸው በደረጃ የተከፋፈሉ መሆኑንና መስፈርቱንም ሌሎች መመዘኛዎችን እንደማያካትት እንዲሁም የደረጃ አመዳደቡ በፕሮጀክት አስፈጻሚዎች ዘንድ እንደማይታወቅ ከተደረገው ቃለምልልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

104. የልማት ፕሮጀክቶችን በባህሪያቸው እና በውስብስብነታቸው መሰረት በደረጃ አለመከፋፈል ከሃብት አመዳደብ እና ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የጊዜ መጠን በእቅድ

ውስጥ ለመገመት ና ለማካተት ስለሚያስቸግር በሃብት እና በጊዜ አመዳደብ እና አጠቃቀም ላይ ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የቅድመ አዋጪነት ጥናት እና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ለትላልቅ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ በመሆኑ ተፈላጊው የጥናት አይነትን ለየትኛው ፕሮጀክት እንደሚያስፈልግ መለየት አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

## ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ጥናት ያልተዘጋጀላቸው የልማት ፕሮጀክቶች ስለመገኘታቸው፣

105. ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ስራ ከመጀመሩ በፊት በፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያው መሰረት የአዋጭነት ጥናት እና የዝርዝር ንድፍ (ዲዛይን) ሥራ ሊዘጋጅለት ይገባል፡፡

106. ይሁን እንጂ የዚህ አይነቱ አሰራር ተፈጻሚ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት፣ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት እና የዲዛይን ጥናት ሳይሰራላቸው ወደ ግንባታ ሥራ የገቡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በናሙና በኦዲት ከታዩት ፕሮጀክቶች ውስጥ የተወሰኑት ብቻ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

107. ከመንገድ ሴክተር ዱር ቤቴ - ሻሁራ በጥር ወር /1997 ዓ.ም. የተጀመረ፣ እና ሻሁራ - ጎለጎ መንገድ ስራ ፕሮጀክቶች የአዋጪነት እና የምህንድስና ዲዛይን ጥናት ያልነበራቸው ሲሆን፣_የኮምቦልቻ-መካነሰላም መንገድ ስራ በየካቲት 1998 ዓ.ም. የተጀመረ ፕሮጀክት ደግሞ የአዋጭነት ጥናት ያልነበረው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

108. ስለሁኔታው ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የፕሮጀክቶች ክትትል እና ግምገማ ቡድን አስተባባሪ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፣ ለዱር ቤቴ - ሻሁራ እና ሻሁራ - ጎለጎ መንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች የአዋጪነት እና የዲዛይን ጥናት ያልተዘጋጀላቸው መሆኑን፣ ለኮምቦልቻ - መካነሰላም መንገድ ሥራ ፕሮጀክት የአዋጪነት ጥናት ያልተዘጋጀለት መሆኑ ትክክል መሆኑን አረጋግጠው፣ ለምን እንዳልተዘጋጀላቸው ግን አልገለጹም፡፡

109. ለመንገድ ሴክተር ፕሮጀክት ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የአዋጭነት ጥናት (የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተጽእኖ ጥናት (Resettlement action plan)፣ እና የሁለተኛው ክፍል የምህንድስና ዲዛይን ጥናት /Detail Design study/ ናቸው፡፡

110. ለመንገድ ሥራ ፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት አለመከናወኑ ፕሮጀክቱ የሚያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲሁም የወጪ እና ጊዜ መጠን ከወዲሁ ለማመልከት አያስችልም፡፡

በተጨማሪም በአካባቢ ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖም በቅድሚያ ለመገንዘብ ስለማያስችል የቅድመ ጥንቃቄና መከላከያ ተግባራትን ለማከናወን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በተለይም በመንገዱ መሰራት ምክንያት ለሚፈናቀሉ ለአካባቢው ማህበረሰብ አባላት የሚሰጠውን የካሳ ክፍያ በቅድሚያ ዝግጅት ስለማይደረግበት በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት ከማህበረሰቡ ጋር አለመግባባት እና የተለያዩ የሥራ ችግሮች ስለሚፈጥር ለፕሮጀክቱ የጊዜ መጓተት እና አላስፈላጊ ወጪ ሊያስከትል ይችላል፡፡

111. የምህንድስና ዲዛይን ዝርዝር ጥናት በቅድሚያ አለማዘጋጀት ደግሞ፣ የሚሰራውን መንገድ ርዝመት፣ ስፋት፣ ጥልቀት፣ መንገዱ የሚያልፍበት አቅጣጫ፣ የሚሰራበት የግንባታ ቁሳቁስና አይነት፣ የድልድይ ደረጃ እና ብዛት የአካባቢውን የአየር ሁኔታ (climatic condition) እና የጂኦሎጂ ጉዳዮች፣ አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ስፍር እና ልኬት እና የሚፈጀውን ጊዜ ከፋፍሎ ለመገንዘብና ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል ከመሆኑም ባሻገር ጥራቱን የጠበቀ ሥራ እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡ የክትትል ቁጥጥርና ግምገማ ሥራም በተገቢው መንገድ እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡

112. ከጤና ሴክተር የሃይጅንና አካባቢ ጤና ትምህርትና ቁጥጥር እና የመድሀኒት አያያዝና አጠቃቀም ማጠናከርያ ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ለብቻው አልተዘጋጀላቸውም፡፡

113. በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የጤና ሴክተር ከፍተኛ የበጀት ባለሙያ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በጤና ሴክተር ያሉ እንደ ሃይጅንና አካባቢ ጤና ትምህርትና ቁጥጥር የመድሀኒት አያያዝና አጠቃቀም ማጠናከርያ የመሳሰሉት በፕሮጀክት ደረጃ የሚታዩ እንዳልሆነ እና ከጤና ልማት ሴክተር ፕሮግራም ሰነድ ተወስዶ በጀት የሚፈቀድለት መሆኑንና ለእያንዳንዱ የካፒታል በጀት የተፈቀደላቸው የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ለብቻው የማይዘጋጅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

114. በበጀት ነጋሪት ጋዜጣ እንደተመለከተነው በጤና ሴክተር ፕሮግራም ስር ያሉ ፕሮጀክቶች ከእርዳታ እና ከአገር ውስጥ ምንጭ በጀት ለብቻቸው የታወጀላቸው ስለሆነ፣ ለበጀትና አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር አስፈላጊ በመሆኑ፣ የኘሮግራም ወይም የፕሮጀክት ጥናቱ እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም፡፡

115. ስለሆነም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የተሟላና የተገመገመ የጥናት ሰነድ ሳይዘጋጅ  በጀት መፍቀድ እና ክፍያ መፈጸሙ ተገቢነት ያለው አሰራር ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>የልማት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እና የገንዘብ መጠን የማይጠናቀቁ ስለመሆኑ፣</u>

116. እያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት ከአቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮች ካልገጠሙ በቀር፣ በተዘጋጀለት የጥናት ሰነድ ላይ በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ሊጀመርና በተያዘለት የጊዜ ገደብ እና የገንዘብ መጠን መሰረት መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እያንዳንዱ ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ሥራውን መጀመሩንና በየደረጃው (phases) ያሉ  ሥራዎችም በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ መጠናቀቃቸውን ለማወቅ አስፈላጊው የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

117. ይሁን እንጂ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 8 የመንገድ ሥራ ፕሮጀክቶች መካከል አምስቱ  በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዳልተጠናቀቁና ተጨማሪ ጊዜ እንደወሰዱ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 1 ቀርቧል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 1</u> በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተጠናቀቁ የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቶችን የሚያሣይ

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ሥም | የፕሮጀክቱ የስራ ዘመን | ፕሮጀክቱ መስከረም 30/2003 ዓ.ም. የሚገኝበት ደረጃ (በመቶኛ) |
|---|---|---|---|
| 1 | ዱር ቤቴ -ሻሁራ | **ከ05/1997 -10/2002ዓ.ም** | **79%** |
| 2 | ኮምቦልቻ-መካነሰላም | **ከ06/1998 - 12/2002ዓ.ም** | **76%** |
| 3 | ግንደወይን-መካነሰላም | **ከ05/1998 -12/2002ዓ.ም** | **45%** |
| 5 | እንዳቶ-ጋሰራ | **ከ06/2000 - 04/2003 ዓ.ም** | **87%** |

118. ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው የዱር ቤቴ -ሻሁራ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት በሰኔ ወር/2002 ዓ.ም. እንደሚጠናቀቅ በእቅድ የተያዘ ቢሆንም፣ በመስከረም 30/2003 ዓ.ም. የነበረው አፈጻጸም 79% እንደሆነ በቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርት የተመለከተ ሲሆን በግንባታ

መሃንዲሱ (በኮንትራክተሩ) አቅም ማነስ ምክንያት የመንገድ ሥራው የተቋረጠ መሆኑ ተገልጿል፡፡

119. የኮምቦልቻ-መካነሰላም መንገድ ሥራ ፕሮጀክት በነሐሴ ወር/2002ዓ.ም. እንደሚጠናቀቅ በእቅድ የተመለከተ ቢሆንም፣ በመስከረም 30/2003 ዓ.ም. የነበረው አፈጻጸም 76% እንደሆነ በቀረበው የፕሮጀክቱ የአፈጻጸም ሪፖርት ተመልክቷል፡፡

120. የመካነሰላም-ግንደወይን መንገድ ሥራ ፕሮጀክት በነሐሴ ወር/2002 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ በእቅድ የተመለከተ ቢሆንም፣ በመስከረም 30/2003 ዓ.ም. የነበረው አፈጻጸም 45% እንደሆነ በቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርት ተመልክቷል፡፡

121. የእንዳቶ-ጋሰራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ጊዜ በታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም. የነበረ ሲሆን፣ ሥራው ባለመጠናቀቁ ወደ ጥቅምት ወር 2004 ዓ.ም. መራዘሙ እንዲሁም በመስከረም 30/2003 ዓ.ም. የነበረው አፈጻጸም 87% እንደሆነ ከአማካሪ መሃንዲሱ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ታውቋል፡፡ እንዲሁም ለግንባታው መጀመሪያ ከተያዘለት የኮንትራት ውል ብር 390,343,766.96 የዋጋ ለውጥ ተደርጎ ወደ ብር 715,153,664.83 ከፍ እንዲል መደረጉን ከአማካሪ መሃንዲሱ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ተገልጿል፡፡ ይህም ከመጀመሪያው የኮንትራት ውል ዋጋ ወደ 83% ያህል ጭማሪ አሳይቷል፡፡



ፎቶ 1 ሥራው ያልተጠናቀቀው የእንዳቶ ጋስራ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት (ህዳር 28 2003)

122. የመንገድ ሥራ ኘሮጀክቶቹ ለምን በተያዘላቸው ጊዜና በጀት እንደማይጠናቀቁ በተሰጠው መልስ፣ የግንደወይን- መካነሰላም የመንገድ ስራ ፕሮጀክት በነሐሴ ወር/2002 ዓ.ም. ሊጠናቀቅ ያልቻለው በዲዛይን ችግር ምክንያት እንደሆነ ከመንገዶች ባለስልጣን የፕሮጀክቶች ክትትል እና ግምገማ አስተባባሪ ጋር ከተደረገ ቃለ ምልልስ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

123. ለእንዳቶ-ጋሰራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት አለመጠናቀቅ የቀረበው ምክንያት ለመንገድ ሥራው በመጀመሪያ ዝርዝር የዲዛይን ስራ በኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ባለቤትነት ከተጠና በኂላ እንደገና እ.ኤ.አ. ግንቦት 2009 ዓ. ም. በሌላ አማካሪ ድርጅት የዲዛይን ክለሳ በመደረጉና ከዚህ ጋር በተያያዘ የስራው መጠን በመጨመሩ ምክንያት መጀመሪያ ከተያዘለት የኮንትራት ውል ብር 390.3 ሚሊዮን ዋጋ ለውጥ ተደርጎ ወደ ብር 715.2

ሚሊዮን ከፍ እንዲል መደረጉንና የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜም ከታህሳስ 2003 ዓ.ም. ወደ ጥቅምት 2004 ዓ.ም. የተራዘመ መሆኑን ከፕሮጀክቱ አማካሪ መሃንዲስ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ተገልጿል፡፡ የመንገድ ፕሮጀክቶች አጠቃላይ ወጪ ሊጨምርና የማጠናቀቂያ ጊዜም የሚራዘምበት ዋናው ምክንያት በዲዛይን ችግር እና የዲዛይን ለውጥ (ክለሳ) እንደሆነ በተጨማሪ አስረድተዋል፡፡

124. እንደዚሁም በውኃ ሀብትና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሥር ከሚካሄዱት ኘሮጀክቶች ውስጥ በኦዲቱ ለናሙና የታዩት ሁለት ኘሮጀክቶች የአፈጻጸሙ ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

125. የከሰም ተንዳሆ የግድብና መስኖ ልማት ግንባታ ፕሮጀክት እ.አ.አ. በ2004 የተጀመረ ሲሆን በወቅቱ 1.669 ቢሊዮን ብር ይፈጃል ተብሎ የተገመተ ቢሆንም፣ እስከ 2002 ዓ.ም. ብቻ ከ3 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደተደረገ ለገ/ኢ/ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ከቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡ አሁንም ሥራው ያልተጠናቀቀና የከሰም ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት 69%፣ የተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት 55% ያህል ብቻ እስከ 2002 በጀት ዓመት የፊዚካል አፈጻጸም መከናወኑን ከውሃ ሃብትና ኢነርጂ ሚኒስቴር የፕሮጀክት አስተባባሪ በቃል የተገለጸልን ሲሆን ይህን የሚገልጽ የአፈጻጸም ሪፖርት ማስረጃ እንዲያቀርቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም፡፡

126. እንደዚሁም ከውሃ ሃብትና ኢነርጂ ሚኒስቴር ፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር ስለሁኔታው በተደረገ ቃለምልልስ የከሰም ተንዳሆ የግድብና መስኖ ልማት ግንባታ ፕሮጀክት ከ17 ዓመት በፊት በተጠና የአዋጪነት ጥናት መሰረት እንዲጀመር በመደረጉ በሥራው ላይ ካስከተለው ችግር የተነሳ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መጠናቀቅ አለመቻሉ ተገልጿል፡፡

127. የቆጋ መስኖ እና ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክትን በተመለከተ ደግሞ ከውሃ ሃብትና ኢነርጂ ሚኒስቴር ኘላንና ኘሮግራም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በተሰጠ መልስ ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መጠናቀቅ ባለመቻሉ ለሁለት ጊዜ ያህል የተራዘመ መሆኑንና ችግሩ የግንባታውን ሥራ ከሚያከናውነው የሥራ ተቋራጭ፣ ብድር ከሚሰጠው የአፍሪካ ልማት ባንክ እና ከመሬት ካሳ ክፍያ ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የተፈጸመውን አጠቃላይ ወጪ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በሚቀርበው የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ ያልተገለጸ መሆኑም ታውቋል፡፡

128. በትምህርት ሴክተር በኦዲቱ የታዩ ኘሮጀክቶችን በተመለከተ ደግሞ፣ የፕሮጀክቶች ሥራ ዘግይቶ የመጀመርና ዘግይቶ የመጨረስ ሁኔታ በመስተዋሉ፣ ስለምክንያቱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የዕቅድና የሃብት ማሰባሰብና ማስተባበር የሥራ ሂደት ባለቤት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ሁኔታው የሚከሰተዉ የአንዳንድ አጋሮች የማስፈጸሚያ ስልት ጥብቅ መሆኑ፣ ከተግባሪዎች በወቅቱ ሪፖርት አለማግኘትና የባለሙያዎች መለዋወጥ ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

129. በግብርና ሴክተር ስር ያሉ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም መጓተትን በተመለከተ ደግሞ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ለስራ መጓተት (መራዘም) ምክንያቶች የግዢ ስርዓት መጓተቱ፣ መረጃዎች በሚፈለገው ፍጥነት ከአስፈፃሚዎች ስለማይሰጡ በየጊዜው ማስተካከያ ለመስጠት ማስቸገሩ፣ በአጋርነት ከሚሰሩት ክልሎች የገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርት በወቅቱ አለመላኩ፣ ከአበዳሪ ድርጅቶች ገንዘብ በወቅቱ አለመለቀቁ፣ በምክንያትነት የሚጠቀሱ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች የፕሮጀክቶች ስራ እንደራሳቸው ባለመቁጠርና እንደተጨማሪ ትርፍ ስራ ማየት ለችግሮቹ እንደምክንያት የሚገለጹ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

130. ይሁን እንጂ ከላይ እንደተመለከተው የተለያዩ ችግሮችና ምክንያቶች የተሰጡ ቢሆንም፣ ኘሮጀክቶች በተያዘላቸው የሥራ ዘመን ውስጥ አለመጠናቀቃቸው ፈርጀ ብዙ ችግሮች ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የእንዳቶ-ጋሰራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት የማጠናቀቂያ ጊዜ በመራዘሙ ከአካባቢው ህብረተሰብ እና ወረዳ መስተዳድር ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት እና በመስክ ኦዲቱ ለመገንዘብ እንደተቻለው የመንገድ ሥራው በወቅቱ ቢጠናቀቅ የአካባቢውን ህዝብ እንቅስቃሴ ሊያሻሽል እና ምርትን ወደ ገበያ በትራንስፖርት ለማድረስ እና ልውውጥ ለማድረግ ያስችል እንደነበር ነው፡፡ ከዚሁ መንገድ ጋር በተያያዘ በባሌ የሚገኘው ድሬ ሼክ ሁሴን በዓል በሚከበርበት ወቅት ከተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በዓሉን ለማክበር ወደ አካባቢው ለሚመጣ ህብረተሰብ የመንገዱ ለትራፊክ ክፍት መሆን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታው ከፍተኛ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በታቀደለት ጊዜ ባለመጠናቀቁ የህዝቡ እንቅስቃሴ እና የገበያ ልውውጥ በእግር ከጋሰራ (ባሌ) እስከ እንዳቶ ከተማ (አርሲ) የሚያደጉት ጉዞ አስቸጋሪ እንደሆነ ነው፡፡ ሥፍራውም ታሪካዊ የቱሪስት መስህብ በመሆኑ ጎብኚዎችን በመሳብ ለቱሪዝም ገቢ መጨመር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታወቃል፡፡

131. የመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በታቀደለት ጊዜ የማይከናወን መሆኑ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት በቅድሚያ ከተወሰነለት የኮንትራት ዋጋ በላይ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ከመሆኑም ባሻገር ከየፕሮጀክቱ ሊገኝ የታሰበውን ግልጋሎትና ጠቀሜታ አዝጋሚ ከማድረጉ ባሻገር ሊያስተጓጉል ይችላል፡፡ ይህም በአገሪቱ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገትን በሚፈለገው ፍጥነትና ብቃት ባለው የሃብት አጠቃቀም እንዳይከናወን እንቅፋት ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ፕሮጀክት ከተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ዘርፎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው፣ ተጽእኖውም ፈርጀ ብዙ እና ሰፊ በመሆኑ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ ከፍተኛ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

## ኘሮጀክቱ አዋጪ መሆን/አለመሆኑ ጥናቱ ተጀምሮ ከፍተኛ ወጪ ከተደረገበት በኂላ የተቋረጠ ኘሮጀክት ስለመኖሩ

132. የልማት ኘሮጀክቶች አዋጪ መሆን ወይም አለመሆናቸው ዝርዝር ጥናቶች ለባለሙያዎች ሲሰጡ ተገቢው ቢጋር (TOR) ሊኖር ይገባል፡፡ ባለሙያውም በተሰጠው ቢጋር መሠረት ለመሥራቱ በየጊዜው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግና የሚከፈለው ገንዘብ በትክክል በተሠራው መጠን ሊሆን ይገባል፡፡

133. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፣ በግብርና ሴክተር ስር ያለው የእንስሳት ሃብት ልማት ማስተር ፕሮጀክት (በእርዳታ) ጥናት፣ የፕሮጀክት ዝግጅቱ ሁለተኛ ደረጃ (phase) ላይ ሲደርስ ተቋርጧል፡፡ ለምን ጥናቱ እንደተቋረጠ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የፕሮጀክቱ ረቂቅ ጥናት ቀርቦ አማካሪው በተሰጠው ቢጋር /TOR/ መሰረት ስራውን ባለማከናወኑ ምክንያት በመንግስት ተቀባይነት ባለማግኘቱ ስራው የተቋረጠ መሆኑንና ስራውን እንደገና መልሶ ለማስጀመር ጥረት ተደርጎም እንዳልተሳካ ተገልጿል፡፡

134. እንደሚታወቀው አገሪቱ በቀንድ ከብት ከአፍሪካ አንደኛ ከአለም 10ኛ ናት፡፡ ስለሆነም የእንስሳት ሀብት ልማት ማስተር ኘላን ኘሮጀክት ጥናት ዋና ዓላማ በሚቀጥሉት 20 ዓመታት በእንስሳት ሃብት ልማት የተቀናጀ ልማት ለማካሄድ ይቻል ዘንድ በወተት፣ በስጋ፣ በማር፣ በቆዳና ሌጦ፣ በጭነት ስበት እንስሳት ልማት ንዑስ ማስተር ፕላን እና አንድ ዋና ማስተር ፕላን ማዘጋጀት ሲሆን በተጨማሪ ማስተር ፕላኑ ሲጠናቀቅ ለመንግስትና ለግል የልማት ሴክተሮች የኢንቨስትመንት ቅደም ተከተሎችን በመለየት

ፕሮጀክቶችን ማዘጋጀት ነው፡፡ ይህንን ሃብት በአግባቡ ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም በቀጣይነት ለማሳደግ የእንስሳት ሃብት ማስተር ፕላን ፕሮጀክት አስፈላጊ መሆኑ ከሰነዶች ተመልክቷል፡፡ ፕሮጀክቱም አገሪቱ ለ20 ዓመት የምትመራበት ማስተር ፕላን ማዘጋጀት እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

135. ይሁን እንጂ ከፕሮጀክቱ ጠቀሜታ አንጻር የዝግጅት ሂደቱ ሁለተኛ ደረጃ (phase) ደርሶ ለጥናት ዝግጅት የሚያስፈልገው ሃብት በ2000 በጀት ዓመት ብር 4,922,220፣ በ2001 በጀት ዓመት ብር 23,480 እና በ2002 በጀት ዓመት ብር 11,630.00 በድምሩ ብር 4,957,330 ወጪ ተደርጎ እንዲቋረጥ መደረጉ ታውቋል፡፡ ስለሆነም በወቅቱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ፣ የወጣው ከፍተኛ ገንዘብ እንዲባክን ከመደረጉም በላይ ሀገሪቱ ለ20 ዓመታት የምትመራበት ማስተር ፕላን አለመዘጋጀቱ ከኘላኑ ተግባራዊነት የሚገኘውን ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚያሳጣ በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>የፕሮጀክቶችን ሥራ በሚከታተሉት ሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች መካከል ተገቢው ቅንጅታዊ አሰራር ስላለመኖሩ፣</u>

136. የልማት ፕሮጀክቶች የቅድመ ትግበራ ግምገማ፣ እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሥራ በሚያከናውኑት የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት እና የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

137. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የቅድመ ትግበራ ሥራ ለመጠናቀቁ የጽሁፍ ማስረጃ ለበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ሳይቀርብ በጀት የሚፈቀድ በመሆኑ፣ በሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች መካከል ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩን ያመለክታል፡፡

138. ስለ ጉዳዩ ሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች ተጠይቀው ከሰጡት መልስ ለመገንዘብ እንደተቻለው የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት እና የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተቀናጅተው ይሰራሉ ለማለት እንደሚያስቸግር በየበኩላቸው ገልጸዋል፡፡ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የበጀት ስርዓቱን ተከትሎ ከመስራት በስተቀር የልማት እቅድን ቴክኒካል ግብአት ለመጠየቅና ለመጠቀም የሚያስችል ስርዓት እንደሌለና ነገር ግን እንደ አሰራር ለአዳዲስ የካፒታል ፕሮጀክቶች ከልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት ቴክኒካል ግብዓት (input) እንደሚያስፈልጋቸው፣ ብዙውን ግዜ የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት ተሳትፎ በጀት በሚሰጥበት ወቅት በአገራዊ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ከተቀመጡ

አቅጣጫዎችና ዋናዋና ግቦች ጋር ያልተሣሰረ በጀት በአስፈጻሚው አካላት የሚቀርብ ከሆነ የማስተካከያ ሃሳብ በማቅረብ ጉዳይ ላይ ብቻ የሚገኙ መሆኑን ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡

139. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለልማት ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የፕሮጀክት ስርዓት እና የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያ በ1998 ዓ.ም. እንዲሁም ለበጀት አፈጻጸም የበጀት ስርዓት (Draft budget manual) በJanuary 12/2007 የተዘጋጀ ቢሆንም፣ የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያው እና የበጀት ማንዋሉ በልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት እና በበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተነጣጥሎ እንደሚተገበር የፕሮጀክት አፈጻጸም መመሪያ እና የበጀት ማኑዋል ተቋማዊ ቅንጅታዊ አሰራር እንዳልያዙ ያመለክታሉ፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ የልማት ፕሮጀክት የጥናት ሰነዶች ለቅድመ ትግበራ ግምገማ ሳይቀርቡ በበጀት ይታቀፋሉ፡፡

140. ስለሆነም አንዳንድ የልማት ፕሮጀክቶች በቅድመ ትግበራ ግምገማ ሳያልፉ በጀት ሊፈቀድላቸው ስለሚችል አሠራሩ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርበው የሩብ ዓመት አፈጻጸም ሪፖርት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የሚቀርብ ስላለመሆኑ፣</u>

141. በፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት ስለ ፕሮጀክቶች የስራ አፈጻጸም በየሶስት ወሩ የክትትልና ግምገማ ውጤት ሪፖርት እየተዘጋጀ ለሚ/ር መ/ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ስለተገኘው የክትትልና የግምገማ ውጤት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየሩብ ዓመቱና በየአመቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ማድረግ አለበት፣

142. ይሁን እንጂ በአስፈጻሚ መ/ቤቶች እየተዘጋጀ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርበውን የፕሮጀክቶች የሩብ ዓመት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም የግምገማ እና የተጠቃለለ ሪፖርትና የግምገማ ውጤት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የማይቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡

143. ስለ ሁኔታው የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ፣ የፕሮጀክት አስፈጻሚዎች የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም የተጠቃለለ ሪፖርት ለሚኒስትሮች ም/ቤት በአሁኑ ወቅት የማይቀርብ መሆኑን፣ ቀደም ባሉት ዓመታት ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ላለው የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ ዴስክ

የአፈጻጸም ሪፖርት ይቀርብና ከመ/ቤቶች ጋር ውይይት ይደረግበት እንደነበርና ሆኖም በአሁኑ ወቅት  የተቋረጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

144. ይሁን እንጂ የሪፖርቱ መቋረጥ የበላይ አካል በገንዘብና ኢኮኖሚ ል/ሚ/ር የተዘጋጀ እና የተገመገመ የፕሮጀክቶችን አጠቃላይ የሥራ ሂደት ሁኔታ የሚያውቅበት እና የሚከታተልበት መንገድ እንደሌለ የሚያሳይ ከመሆኑም በተጨማሪም ከፕሮጀክት አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ የተለያዩ ችግሮችን ለበላይ አካል ቀርቦ እልባት እንዳያገኙ ያደርጋል፡፡

145. ስለሆነም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርብለትን የፕሮጀክቶች የሩብ ዓመት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም  የግምገማ እና የተጠቃለለ ሪፖርት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ሆኖ ሳለና ተጠቃሚው ክፍል እንዳይላክ ሳይጠይቅ እንዲቋረጥ መደረጉ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚቀርበው የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት ይዘት ወጥነት የሌለውና በፕሮጀክት ክትትል መመሪያው መሰረት  ስላለመሆኑ፣</u>

146. የፕሮጀክት አስፈጻሚዎች በጸደቀው የፕሮጀክት ሰነድ መሰረት፣ በፕሮጀክት የድርጊት መርሃ ግብር፣ በክትትልና ግምገማ መመሪያ እንዲሁም በሥምምነቶች መሠረት በትክክል የፕሮጀክቱን የስራ ሂደት፣ ግብዓት፣ ውጤት፣ ስኬት እንዲሁም የፕሮጀክቱን ፋይዳ (impact) በመከታተል በየ3 ወሩ ለ/ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

147. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው፣ በዚህ የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ በኩል የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በጥሩ ተሞክሮ የሚገለጽ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የበጀት ባለሙያ ጋር በተደረገው ቃለ ምልልስ እና ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከቀረቡት የአፈጻጸም ሪፖርቶች እንደተገነዘብነው የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ አመት ብቻ ሳይሆን በየወሩ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሚያቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡

148. የሌሎች ሴክተሮች የሪፖርት አቀራረብ ሲታይ፣ ከጤና ሴክተር፣ ከትምህርት ሴክተር እና ከግብርና ሴክተር አስፈጻሚዎች ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሚቀርበው የፕሮጀክት የፊዚካል እና

የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት በሚ/ር መ/ቤቱ በተዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ (ፎርማት) መሰረት አለመሆኑ ታውቋል፡፡ የሚቀርበው ሪፖርትም በየሩብ አመቱ መሆን ሲገባው፣ በየ6 ወር ወይም በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

149. ለምሳሌ በመስክ ጉብኝቱ በናሙና ከታዩ የአፈጻጸም ሪፖርቶች የሃረሪ ክልል ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ባዘጋጀው የ2002 በጀት ዓመት ማጠቃለያ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ላይ የአመቱ የፊዚካል አፈጻጸም በአመቱ ከታቀዱ ስራዎች ጋር ተገናዝቦ አልቀረበም፡፡ የግብርና ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር በስራቸው የሚያከናውኗቸውን ፕሮጀክቶች እና የሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ማጠናከሪያ ፕሮጀክት የፋይናንሻል እና የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በየሩብ አመቱ የማያቀርቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

150. እንዲሁም ለሚ/ር መ/ቤቱ ከቀረበው የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት በጤና ልማት ሴክተር ፕሮግራም ስር ያሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ለምሳሌ ለመድሀኒት አያያዝና አጠቃቀም ማጠናከር እና ለሃይጅንና አካባቢ ጤና ትምህርትና ቁጥጥር የመሳሰሉት ለየብቻቸው በነጋሪት ጋዜጣ የካፒታል በጀት ታውጆላቸው እያለ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በቀረበው የፋይናንሻል አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የእያንዳንዱን ፕሮጀክት የፋይናንሻል ክንውን አያሳይም፡፡ በተጨማሪም ከመንገድ ሴክተር፣ ከውሃ ሴክተር፣ ከትምህርት ሴክተር እና ከግብርና ሴክተር አስፈጻሚዎች ከቀረበው የአፈጻጸም ሪፖርት ለመገንዘብ እንደተቻለው የሚቀርበው የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት በፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ መመሪያ ላይ በተመለከተው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ (format) መሰረት የፕሮጀክቶችን አጠቃላይ የፋይናንስ ክንውን ማሳየት ሲገባው ተግባራዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

151. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የበጀት ባለሙያ የአፈጻጸም ሪፖርት አቀራረቡ በፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ መመሪያ መሰረት ስላልሆነበት ምክንያት ተጠይቀው በሰጡት መልስ አስፈጻሚዎች ለጉዳዩ ትኩረት ካለመስጠት የተነሳ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

152. አስፈጻሚዎች በየሩብ ዓመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት የማያቀርቡበትን ምክንያት አስመልክቶ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ አስፈጻሚዎች ዓመታዊ ሪፖርት የሚያቀርቡና በየሩብ አመቱ የማያቀርቡ መሆኑን

አረጋግጠዋል፡፡ በመቀጠልም በሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅም መውሰድ የሚቻለው እርምጃ በጀት መከልከል ብቻ ስለሆነ እርምጃው ህብረተሰቡን ስለሚጎዳ ተፈጻሚ አለመደረጉንና በየጊዜው የቃል ማሳሰቢያ በመሥጠት ሲታለፍ እንደቆየ% እንደዚሁም የአስፈጻሚ መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በሚገኙበት በጀት መስሚያ (budget hearing) ጉባኤ ስብሰባ ላይ ተጨማሪ ማሳሰቢያ እንደሚሰጥ አስታውቀዋል፡፡

153. ይሁን እንጂ ከተሰጡት መልሶች በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ የተወሰኑ ጥረቶች የተደረጉ መሆኑ ቢገለጽም፣ የክትትሉና የማስፈፀም ስልቱ ደካማ በመሆኑ የቁጥጥር ሥርዓቱ ልል መሆኑን ያመላክታል፡፡

<u>የፕሮጀክቶች አተገባበር ሂደትን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የሚከናወነው የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የተቋረጠ ስለመሆኑ፣</u>

154. የልማት ፕሮጀክቶች አተገባበር ሂደት አፈጻጸምን አስመልክቶ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የግምገማ ስራ ሊያከናውንና ስለውጤቱም ሪፖርት በማዘጋጀት ለበላይ አካል የሚቀርብበት ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

155. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ እንደተቻለው የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶችን፣ የትምህርት ሴክተር ፕሮጀክቶችን፣ የግብርና ሴክተር ፕሮጀክቶችን እና የጤና ሴክተር ፕሮጀክቶችን የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ከየፕሮጀክቱ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የክትትል እና የማጠናቀቂያ ግምገማ (monitoring and completion evaluation) የማይከናወን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

156. ስለሁኔታው በሚኒስቴር መ/ቤቱ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ የበጀት ባለሙያዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከባለድርሻ አካላት ጋር ክትትል እና የማጠናቀቂያ ግምገማ የማድረግ ስርዓቱ በፊት እንደነበረና አሁን ግን እንደሌለ አስታውቀው% በመቀጠልም በአሁኑ ወቅት ከውሃ ሴክተር ፕሮጀክቶች በቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ላይ ብቻ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በክትትልና ግምገማ ሥራ ላይ ተሳትፎ መኖሩን ገልጸው፣ አሠራሩም በቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት እስቲሪንግ ኮሚቴ (steering committee) ውስጥ የፊዚካል እና የፋይናንስ አፈጻጸም ጉዳይን በሚገመግመው ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከክልል፣ የአካባቢ ሰዎች እና ባለድርሻ አካላት የሚገኙበት መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

157. በመሠረቱ የፕሮጀክቶች የትግበራ ሂደትና ማጠናቀቂያ ግምገማዎች (On-going and Terminal Evaluation) ፕሮጀክቶችን በባለቤትነት ከሚተገብሩ የክፍላተ ኢኮኖሚ አስፈጻሚ መ/ቤቶች፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው የልማት አጋር ድርጅቶች በሚውጣጡ ባለሙያዎች (የግምገማ ቡድን) ማከናወን የሚገባ ሲሆን ይህም የባለድርሻ አካላትን በፕሮጀክቱ የሥራ ሂደት ያላቸውን ግንዛቤ እና ሚና እንዲጨምር በማድረግ ለፕሮጀክቱ ውጤታማነት እና ስኬታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ስለሚያደርግ የነበረው ሥርዓት እንዲቋረጥ መደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>በክትትል እና ግምገማ ወቅት የታዩ እና መስተካከል የሚገባቸው ስራዎች  በፕሮጀክት አስፈጻሚው አካል  በትክክል ለመስተካከሉ  የሚረጋገጥበት ሥርዓት ስላለመኖሩ፣</u>

**158.** የገ/ኢ/ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ከአስፈጻሚ መ/ቤቶች እየተዘጋጁ የሚቀርቡለትን የፊዚካል እና ፋይናንሻል አፈጻጸም ሪፖርቶችን መገምገም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በመስክ በመገኘት የተከናወኑ ስራዎችን መጎብኘት ይገባዋል፡፡ በግምገማውና በጉብኝቱ ውጤት መሰረት መስተካከሉንም የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

**159.** ይሁን እንጂ በኦዲቱ እንደታወቀው፣ የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶችን  በክትትል እና ግምገማ ወቅት የታዩ እና መስተካከል የሚገባቸው ስራዎች  በፕሮጀክት አስፈጻሚው አካል በትክክል ለመስተካከሉ  የሚረጋገጥበት ስርዓት  አለመኖሩ፣ የግብርና ሴክተር ፕሮጀክቶች ላይ ደግሞ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች በበጀት መስሚያ ወቅት ከሚነሱ በስተቀር በክትትል እና ግምገማ ወቅት ስለታዩ እና መስተካከል ስለሚገባቸው ስራዎች  በፕሮጀክት አስፈጻሚው አካል ስለመስተካከላቸው እንደ ስርዓት እየተሰራበት እንዳልሆነ፣ ተረጋግጧል፡፡

160. ስለሁኔታው ከበጀት ዝግጅት እና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በተሰጠው መልስ በበጀት ዝግጅት ወቅት በአፈጻጸም ላይ የነበሩ ችግሮች መፈታታቸውን እና በቀጣይ የተደረጉ ዝግጅቶች እንዲዳሰሱ እንደሚደረግ፣ እንደዚሁም የበጀት ዝውውር  በሚጠየቅበት ወቅት የሚፈቀደው አፈጻጸሙ ምን እንደሚመስል በበጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬቱ የሚታይ መሆኑን ገልጸው፣ በመቀጠልም ከፊዚካል አፈጻጸም የሚታይ ክፍተትን የመከታተል ሥራ ብዙም ትኩረት ተሰጥቶት የማይከናወን በመሆኑ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የማስተካከያ ስራ እንደማይሰራ አስታውቀዋል፡፡

161. ስለሆነም በክትትል፣ በግምገማና በጉብኝት ወቅት የተገኙ ግኝቶች መስተካከላቸው አለመረጋገጡ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ከአስፈጻሚዎች የሚቀርበው የአፈጻጸም ሪፖርት የፕሮጀክቱን አጠቃላይ የፋይናንስ እና የፊዚካል ክንውን የሚያካትት ስላለመሆኑ</u>

162. በአስፈጻሚ መ/ቤቶች እየተዘጋጁ የሚቀርቡ የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርቶች በይዘታቸው የተሟሉ፣ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የሚቀርቡ፣ የማያሻሙ እና ግልጽነት ያላቸው፣ ኘሮጀክቶቹ ከተጀመሩ ጀምሮና የአሁኑን የፋይናንስ እና የፊዚካል ክንውን መጠን በበቂ መረጃ የተደገፉና ሊለኩ የሚችሉ እንዲሁም ለበላይ አካላት ውሳኔ መስጠት የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

163. ይሁን እንጂ በኦዲቱ፣ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚቀርቡ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ይዘት ለመገንዘብ እንደተቻለው ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የሚቀርበው የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ የፊዚካል አፈጻጸሙ ከጠቅላላው ምን ያህል እንደተከናወነ የሚያሳይ ሲሆን፣ የፋይናንስ አፈጻጸሙን ግን በሩብ ዓመቱ የተፈጸመውን የፋይናንስ ክንውን ብቻ እንጂ ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን አጠቃላይ የፋይናንስ ክንውን አያሳዩም፡፡ እንዲሁም ከውሃ ሴክተር፣ ከትምህርት ሴክተር፣ ከጤና ሴክተር እና ከግብርና ሴክተር በአስፈጻሚዎች በሚቀርበው የአፈጻጸም ሪፖርት ላይ የተመለከተው የወቅቱን ብቻ እንጂ አጠቃላይ የፊዚካል እና የፋይናንስ አፈጻጸም ክንውንን የሚያመለክት ሆኖ አልተገኘም፡፡ አሠራሩ በአጠቃላይ ሲታይ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀውን የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ (መመሪያ) ያልተከተለና አስፈጻሚው መ/ቤት በሚፈልገው መሠረት የሚላኩ መሆናቸው ታውቋል፡፡

164. ስለሆነም አጠቃላይ የፕሮጀክቱ የፋይናንስና የፊዚካል ክንውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ካልቀረበ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግና ለውሳኔ አሰጣጥም የሚያስቸግር መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

<u>በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚዘጋጀው መረጃ ተመሳሳይ ስላለመሆኑ</u>

165. የእያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት የኮንትራት ዋጋ እና የፋይናንስና የፊዚካል አፈጻጸም መረጃዎች እና የኘሮጀክት የኮንትራት ዋጋ በአስፈጻሚ መ/ቤቶች እና በገ/ኢ/ል/ሚ/ር

ተመሣሣይ ሊሆኑ ይገባል። ልዩነቶች ቢከሰቱ በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመሥርተው በየወቅቱ ሊስተካከሉ ይገባል።

166. ይሁን እንጂ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ የታዩ 8 ኘሮጀክቶች የኘሮጀክቶች የኮንትራት ዋጋ ከብር 18 ሚሊዮን እስከ ብር 496 ሚልዮን ልዩነት ያለባቸው ሆነው የተገኙ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና በገ/ኢ/ል/ሚ/ር በየበኩላቸው የተያዘው የፕሮጀክቶች የኮንትራት ዋጋ ደግሞ ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል። ዝርዝር ሁኔታውም እንደሚከተለው ቀርቧል።

167. <u>ሠንጠረዥ 2 በገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በተገኘ መረጃ መሰረት የታየ የፕሮጀክቶች የኮንትራክት ዋጋ ልዩነት</u>

| ተቁ | የፕሮጀክቱ ስም | በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የተመለከተ የኮንትራት ዋጋ(ብር) | በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተመለከተ የኮንትራት ዋጋ (ብር) | ልዩነት (ብር) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ዱር ቤቴ-ሻኑራ | 147,532,000 | 128,049,228.29 | 19,482,772.00 |
| 2 | ሻሁራ- ጎለጎ | 360,476,000 | 341,479,872.50 | 18,996,127.50 |
| 3 | ኮምቦልቻ-መካነሰላም | 738,178,000 | 694,149,063.23 | 44,028,936.77 |
| 4 | መካነሰላም-ግንደወይን | 955,337,000 | 904,244,638.85 | 51,092,361.15 |
| 5 | እንዳቶ-ጋሰራ | 408,344,000 | 390,343,766.96 (ከዲዛይን ክለሳ በኋላ 715,153,664.83) | 18,000,233.04 (ከዲዛይን ክለሳ በኋላ -306,809,664.83) |
| 6 | አዲረመት -ደጀና-ዳንሻ | 430,000,000 | 926,292,277.49 | -496,292,277.49 |
| 7 | እንዳስላሴ-ደደቢት | 491,000,000 | 510,670,201.45 | -19,670,201.45 |
| 8 | ደደቢት-አዲረመጥ | 420,000,000 | 801,212,552.61 | -381,212,552.61 |

168. በመረጃዎቹ ላይ ለምን ልዩነቶች እንደሚፈጠሩ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት አስተያየት “የፕሮጀክቶች የኮንትራት ዋጋ በተለያየ ምክንያት ሊከለስ ይችላል” የሚል መልስ ሰጥተዋል።

169. በተጨማሪም የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ደረጃን አስመልክቶ በሁለቱ መ/ቤቶች ያለው መረጃ ተመሳሳይ አለመሆኑ ታውቋል፡፡ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የእንዳቶ-ጋሰራ መንገድ ስራ ፕሮጀክትን ብቻ በምሳሌነት ብንወስድ፣ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እስከ መስከረም 30/2003 ዓ.ም. በቀረበው የፊዚካል አፈጻጸም ሪፖርት መሰረት 52 ኪ.ሜ. ( 87%) እንደተከናወነ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን የአማካሪ መሃንዲሱ መረጃ ደግሞ 49.22 ኪ.ሜ (81.66%) ተመዝግቧል፡፡ ከሁለቱም አካሎች የተለያየ የአፈጻጸም ሪፖርት በመገኘቱ፣ ስለልዩነቱ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው፣ ዝርዝር ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ መልስ ተሠጥቶበታል የሚል አስተያየት ብቻ ሰጥተዋል፡፡

170. ከላይ የተጠቀሰውን የእንዳቶ- ጋሰራ መንገድ ስራ ፕሮጀክት በመስክ ጉብኝት ወቅት በአካል በመመልከት ከአማካሪ መሃንዲሱ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለመገንዘብ እንደተቻለው፣ የተጠናቀቀው መንገድ እርዝመት በመስከረም 30/2003 ዓ.ም. ያለው የፊዚካል አፈጻጸም 81.66% እንደሆነ ነገር ግን የተጠናቀቀውን መንገድ በርዝመት እንዳልተለካና የፋይናንስ አፈጻጸምን መሰረት በማድረግ 49.22 ኪ.ሜ የስራ አፈጻጸም የተመዘገበ መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም ከሥራ ተቋራጩ መሃንዲስ ጋር በተደረገ ቃለምልልስ ደግሞ 82.08% የፊዚካል አፈጻጸም እንደተመዘገበ ተገልጿል፡፡

171. በመስክ ጉብኝት ወቅት የዚህን መንገድ ሥራ በመመልከት ለመገንዘብ እንደተቻለው የመንገድ ስራው በመስከረም 30/2003 ዓ.ም. 52 ኪ.ሜ (87%) ያህል መንገድ ለመከናወኑ መቀበል አያስደፍርም፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት በኦዲቱ ጉብኝት የተደረገው በታህሳስ/2003 መጨረሻ ሪፖርቱ ከቀረበ ከ 3 ወራት በኋላ የመንገዱ ሥራ ሲታይ፣ የተሠራው የጥርጊያ መንገድ የተወሰኑ እርዝመቶች ያልተጠረጉ፣ የሥራው አካሄድም የተወሰኑ አካባቢዎችን የመሥራት እና ወደ ሌላ አካባቢ በመሄድ የተቆራረጠ አሠራር በመሆኑ የተጠናቀቁ ወይም በመጠናቀቅ ላይ ያሉ ተብለው ለመለካት የሚያስቸግሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡



ፎቶ 2፡ ገና በመሠራት ላይ ያለ የእንዳቶ ጋሰራ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት የሚያሳይ ፎቶ



ፎቶ 3፡ በእንዳቶ ጋሰራ መንገድ ሥራ በዋቤ ወንዝ ላይ እየተሰራ የሚገኘውን ድልድይ የሚያሳይ ፎቶ

172. በየትኛውም አካል የሚዘጋጅ መረጃ ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ፣ ተለክቶ፣ ተመዝኖና ተሰልቶ ወቅታዊ ሁኔታን የሚያሳይ፣ ለውሳኔ አሰጣጥ፣ ለክትትልና ቁጥጥርም ግብዓት መሆን የሚችል መሆን ሲገባው በአንድ ኘሮጀክት ላይ የተለያየ መሆኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>ለፕሮጀክቶች ከመነሻ ጥናት ጀምሮ እስከ ፍጻሜና ድኅረ ትግበራ ያለውን መረጃ ለማጠናቀርና ለመጠበቅ የሚያስችል የተዘረጋ ና ተግባራዊ የሆነ ስርዓት ስላለመኖሩ</u>

173. የልማት ፕሮጀክቶች ከመነሻ ጥናት ጀምሮ እስከ ፍጻሜና ትግበራ ውጤት ያለውን ሂደትና ዝርዝር ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ ሊዘጋጅ፣ ሊጠናቀርና ለሌሎች ለወደፊት ለሚሠሩ ኘሮጀክቶች ግብዐት ሊሆን በሚችል መልኩ ሊጠበቅ ይገባል፡፡ እነኚህ መረጃዎች በገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና በአስፈጻሚዎች ሊያዙ ይገባቸዋል፡፡

174. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እነዚህ መረጃዎች እንዲቀርቡልን ተጠይቀው በሁለቱም አካላት የሚጠናቀሩበትና የሚጠበቁበት ሥርዓት ባለመኖሩ የሌሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ለመረጃም ያህል በኦዲቱ በናሙና በታዩ ኘሮጀክቶች ለተመለከተው ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

175. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት መረጃዎች እንዳሉ ቢገለጽም በኦዲት ናሙና ካየናቸው የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለእንዳቶ -ጋሰራ የመጀመሪያ የዲዛይን ጥናት የሌለ መሆኑ፣ የእንዳስላሴ- ደጀና -ዳንሻ መንገድ ሥራ የዲዛይን ጥናት አለመገኘቱ፣ ኮምቦልቻ- መካነሰላም መንገድ ስራ የዲዛይን ጥናት ከተሰራ የቆየ ነው በማለት አለመገኘቱ እና ለኦዲት ሊቀርብ አለመቻሉ፣

176. በገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር የትራዠሪ ዳይሬክቶሬት ከመንገድ ሴክተር ለዱር ቤቴ-ሻሁራ፣ ሻሁራ-ጎለጎ የመንገድ ስራ ፕሮጀክት፣ እንዳ ስላሴ -ደጀና -ዳንሻ የመንገድ ስራ፣ ግንደ ወይን -መካነሰላም-ኮምቦልቻ የመንገድ ስራ እና እንዳቶ-ጋሰራ የመንገድ ስራ ፕሮጀክቶች ሥራ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ጥቅምት 30 2003 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ለፕሮጀክቶች የተፈጸመ አጠቃላይ ክፍያን የሚያሳይ መረጃ ለኦዲቱ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አለመቻሉ፣

177. የውሃ ሴክተር ፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶችና የተጠናቀሩ መረጃዎች በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለኦዲቱ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ ከውሃ ሃብት ሚኒስቴር በቃለምልልስ እንደገለጹት የመረጃ አያያዝን ለማጠናከር ከዚህ ቀደም የተዘረጋ ስርዓት አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

178. ከውሃ ልማት ሴክተር የመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት፣ የቆጋ የመስኖ ልማትና ተፋሰስ እንክብካቤ ፕሮጀክት እና ለከሰም ተንዳሆ ግድብእና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ለእያንዳንዱ የትግበራ ስራ ከተጀመረ ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30/2003 ዓ.ም. ድረስ ለፕሮጀክቶቹ የተፈጸመ አጠቃላይ ክፍያን የሚሳይ መረጃ ትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት እንዳለው ተጠይቆ ሊያቀርብ አለመቻሉ፣

179. ስለሆነም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የእያንዳንዱን ፕሮጀክት የክፍያ መረጃ መያዙ ለየፕሮጀክቱ የሚፈፀመው ክፍያ ከኮንትራት ዋጋ በላይ እንዳይሆን መቆጣጠሪያ መንገድ ሆኖ ሳለ ተፈጻሚ ሳይሆን ተገኝቷል፡፡ ይህን መረጃ አለመያዙ ለፕሮጀክቶች ከኮንትራት ውል ዋጋ

በላይ ክፍያ እንዲፈጸም ያደርገዋል፡፡ ለዚህም የእንዳቶ ጋሰራ መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ከመጀመሪያ የተገባው የፕሮጀክት የኮንትራት ውል ብር 390, 347,766.96 ሲሆን ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ፕሮጀክት ፕሮፋይል የተገኘው የፕሮጀክት ዋጋ መረጃ የሚያመለክተው ደግሞ ብር **408,344,000.00** መሆኑን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ለዚሁ ፕሮጀክት በትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ከ2000 በጀት ዓመት እስከ ጥቅምት 30 /2003 ዓ.ም. የተፈጸመ ክፍያ በድምሩ ብር 649,553,938.00 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ሁኔታ ለመገንዘብ የሚቻለው አስተማማኝ የሆነ መረጃ ለማግኘት የማያስችል መሆኑን ነው፡፡

<u>ለልማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በየደረጃው የሚለቀቀው ተጨማሪ ገንዘብ ቀደም ብሎ የተፈቀደው በትክክል በሥራ ላይ መዋሉ ሳይረጋገጥ ስለመሆኑ፣</u>

180. የፕሮጀክቶች አስፈጻሚ አካላት በየደረጃው እንዲለቀቅላቸው ለሚጠይቁት ገንዘብ በቅድሚያ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት (የፋይናንስና የፊዚካል) እንዲያቀርቡ መደረግ አለበት፡፡ እንዲሁም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ገንዘብ በየደረጃው (phases) ከመልቀቁ በፊት የክትትልና ግምገማ ስራ (የመስክ ስራን ጨምሮ) በማከናወን ሪፖርት ማዘጋጀትና ለቀጣይ ስራ ገንዘብ እንዲለቀቅ በጽሁፍ ለትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ አለበት፡፡ የትሬዠሪ ዳይሬክቶሬትም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ቀደም ብሎ የተፈቀደው በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ከገመገመ በኂላ ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

181. ይሁን እንጂ የትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ለካፒታል ፕሮጀክቶች ክፍያ በሚፈጽምበት ወቅት የፕሮጀክቶች የፊዚካል እና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት ግምገማ አለማከናወኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

182. ስለሁኔታው ከትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እንደተገለጸው፣ የእርዳታና ብድር ሂሳብ ከሆነ እንደሚገመግሙት፣ በአገር ውስጥ ለሚሸፈኑት ፕሮጀክቶች ደግሞ በጥቅል (lump sum) ለሚያከናውኑት ፕሮጀክቶች የወሰዱትን ጠቅላላ ገንዘብ ስራ ላይ ማዋላቸውን እንደሚያዩ ገልጸዋል፡፡

183. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ከተለያዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የቀረቡ ዶኩመንቶች ሲታዩ በእርዳታ እና ብድር ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ለመንግስታት ትብብር ዳይሬክቶሬት የፋይናንሻል አፈጻጸም ተብሎ የሚቀርበው ሪፖርት ለጋሾች ለአስፈጻሚዎች የከፈሉት የገንዘብ መጠን እንጂ ሥራ ላይ ስለዋለው የአፈጻጸም ሪፖርት አለመሆኑን፣ በአገር ውስጥ

ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶችም ከባንክ አካውንታቸው የወሰዱት ከባንክ በየቀኑ በሚመጣ ሪፖርት እንጂ የፋይናንሻል አፈጻጸሙን የማያሳይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ከባንክ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ በትክክል ሥራ ላይ ለመዋሉ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የማይረጋገጥ መሆኑን ነው፡፡

184. ስለሆነም፣ ለፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በጀት ከጸደቀ በኋላ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተፈቅዶ ወጪ የተደረገ ገንዘብ፣ ለታቀደለት ዓላማ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን የሚያረጋግጥ መረጃ በየጊዜው ከፕሮጀክት አስፈጻሚው መ/ቤት በሪፖርት መልክ ቀርቦና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ግምገማ ተከናውኖ ተጨማሪ ክፍያ እንዲለቀቅ የማይደረግ ከሆነ፣ የገንዘብ አጠቃቀሙን ለማወቅ የማይቻል በመሆኑ አሠራሩን ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>*ሥራቸው ለተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የድህረ ትግበራ ግምገማ የማይከናወን ስለመሆኑ፣*</u>

185. ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋጽኦ አላቸው ተብለው በተለዩት ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ (ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ሥራ ከጀመረ ጥቂት ዓመታት በኋላ ቀደም ብለው በተቀመጡ የፕሮጀክቱ በአካባቢ ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት ተጨማሪ ፋይዳ መሠረት፣ የተገኙ የግብ ስኬቶች እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች) ሊካሄድ ይገባል፡፡

186. ከፍተኛ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አስተዋጽኦ አላቸው ተብሎ በሚታመንባቸው ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ ማካሄድ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ በዚህ የፕሮጀክት ዑደት ቀደም ብለው በተቀመጡ የፕሮጀክት ዓላማዎች መሰረት የተገኙ የግብ ስኬቶችን እና ኢኮኖሚያዊ/ማህበራዊ ለውጦችን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

187. ስለሆነም በልማት ኘሮጀክቶች የድህረ ትግበራ ግምገማ በየሴክተሩ ይደረግ እንደሆነ ለማወቅ በተደረገው ኦዲት

188. ከትምህርት ሴክተር ጋር በተያያዘ የኘሮጀክቶች ባህሪ የተለየ በመሆኑ፣ የድህረ ትግበራ ግምገማ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ የሚደረግ መሆኑን ከትምህርት ሚኒስቴር የእቅድና ሃብት ማሰባሰቢያ የስራ ሂደት ባለቤት ተጠይቀው በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡ በመቀጠልም በመንግስት በጀትም የተለያዩ ድጋፎች በትምህርቱ ሰርአት ላይ አስተዋጾ በማድረጉ የትምህርት ሽፋን የጨመረ ስለሆነ፣ የትምህርት ጥራት ግምገማ (National learning assessment) በ4ኛና በ8ኛ እንዲሁም ለመጀመሪያ ጊዜ በከፍተኛ 2ኛ ደረጃ በመካሄዱ፣

በግምገማው ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ትኩረታቸዉን የትምህርት ጥራት ላይ እንዲያደርጉ መደረጉን ለማስረጃነት ጠቅሰዋል፡፡

189. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የውሃ ሃብት ሚኒስቴር፣ የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የግብርና ሚኒስቴር በተጠናቀቁና አገልግሎት መስጠት በጀመሩ ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ (ex-post evaluation) የማይከናወን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

190. ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የክትትል እና ግምገማ ቡድን አስተባባሪ ስለ ድህረ ትግበራ ግምገማ ሲገልጹ ካለው የባለሙያ እጥረት አንጻር የድህረ ትግበራ ግምገማ ማድረግ አለመቻላቸውን ገልጸው፣ ወደፊት ለመስራት በእቅድ መያዙን አብራርተዋል፡፡

191. የውሀ ሃብት ሚኒስቴር ፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሰጡት አስተያየት፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እስካሁን የተጠናቀቀ ፕሮጀክት አለመኖሩን፣ የድህረ ትግበራ ግምገማ ሥራው በሀገር ደረጃ ያልተሰራ ቢሆንም መሰራት እንዳለበት በመታመኑ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ እንዲጀመር ፍላጎት ያለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

192. የግብርና ሚኒስቴር የፕላን እና ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በተጠናቀቁ እና አገልግሎት መስጠት በጀመሩ ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ የማከናወን ተሞክሮ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡ የሃሮማያ ዩኒቨርሲቲ ፕላንና ፕሮግራም ምክትል ኦፊሰር በቃለ ምልልስ እንደገለጹት በዩኒቨርሲቲው የድህረ ትግበራ ግምገማ የማከናወኛ መስፈርት አለመዘጋጀቱንና አለመሠራቱን ገልጸዋል፡፡

# <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

<u>የፕሮጀክቶች አፈጻጸምና ክትትል መመሪያ በበርካታ የፕሮጀክት አስፈጻሚዎች ተግባራዊ ላለመደረጉና ሥልጠና ስላለመሠጠቱ፣</u>

193. አስፈፃሚ አካላት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀውን የፕሮጀክት አዘገጃጀት፣ ቅድመ ትግበራ ግምገማ፣ ክትትል እና ግምገማ መመሪያን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት የገንዘብና ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ ማስተላለፍና ተግባራዊነቱንም መከታተል ይኖርበታል፡፡

<u>በርካታ የልማት ፕሮጀክቶች የትግበራ ስራ ከመጀመራቸው በፊት የፕሮጀክት የቅድመ ትግበራ ግምገማ (appraisal) የማይደረግላቸው ስለመሆኑ፣</u>

194. የልማት ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ/ትግበራ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የቅድመ ትግበራ ግምገማ መመሪያን በመጠቀም የቴክኒካዊ፣ አካባቢ ልማትና ጥበቃ፣ ማህበራዊ፣ ተቋማዊ፣ ፋይናንስ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች መገምገም ይኖርባቸዋል፡፡

<u>በቅድመ ትግበራ ግምገማ የተሰጡ የማሻሻያ ነጥቦች በፕሮጀክት ሰነድ ላይ የተካተቱ መሆናቸው የማይረጋገጥ ስለመሆኑ፡-</u>

195. የቅድመ ትግበራ ግምገማ ማከናወን ያስፈለገበትን አላማ ከግብ ለማድረስ እና ሚ/ር መሥሪያ ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በትክክል ለመወጣት እንዲያስችለው በቅድመ ትግበራ ግምገማ ወቅት የተሰጡ የማሻሻያ ነጥቦች በሙሉ በተባለው መሠረት መካተታቸው መስተካከላቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

<u>በቅድመ ትግበራ ግምገማ አስተያየት የተሰጠባቸው የፕሮጀክት ሰነዶች ተስተካክለው የሚቀርቡበት የጊዜ ገደብ ስላለመኖሩ፣</u>

196. የቅድመ ትግበራ ግምገማ የተደረገላቸው የፕሮጀክት ሰነዶች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ተስተካክለው ለዳግመኛ ፍተሻ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረብ እንዳለባቸው የጊዜ ገደብ እንዲወሰንለትና አስፈፃሚ መ/ቤቶች እንዲያውቁት መደረግ ይገባዋል፡፡

**<u>በፕሮጀክቶች የጥናት ሰነዶች የባለድርሻ አካላት ሚና የማይገለፅና ተገቢው የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ስለመደረጉ የማይረጋገጥ ስለመሆኑ፣</u>**

197. በእያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክት ላይ ተሣታፊ የሚሆኑ ባለድርሻ አካላት (Stakeholders) በዝርዝር ተለይተውና ኃላፊነታቸው ተግልጾ ለቅድመ ትግበራ በሚቀርበው የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ላይ መካተቱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (Environmental impact assessment) ጥናት የሚያስፈልጋቸው የፕሮጀክት አይነቶችም ተለይተው እንዲታወቁና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ውጤትም በሚመለከተው አካል ፀድቆ መቅረቡ መረጋገጥ አለበት፡፡

**<u>የልማት ፕሮጀክቶች ደረጃ የሚሰጣቸው በሚመደበው የገንዘብ መጠን ብቻ ስለመሆኑ፣</u>**

198. የልማት ፕሮጀክቶችን ደረጃ ለመለየትና በፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ጉዳዮች ለምሣሌ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የመሣሠሉትን ለመወሰን እንዲያስችል በፕሮጀክቶች ደረጃ አሠጣጥ ላይ ከገንዘብ መጠን በተጨማሪ ሌሎች መሥፈርቶች የሚካተቱበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

**<u>ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የተሟላ ጥናት ያልተዘጋጀላቸው የልማት ፕሮጀክቶች ስለመገኘታቸው፣</u>**

199. ለማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ወደ ግንባታ/ትግበራ እንዲገባ የሚያስችለው የመንግሥት በጀት ከመፈቀዱ በፊት የአዋጭነት ጥናት እንዲሁም እንደ ፕሮጀክቱ አይነት እየተለየ የዝርዝር ንድፍ (Design) መቅረቡ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፡፡

**<u>የልማት ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እና የገንዘብ መጠን የማይጠናቀቁ ስለመሆኑ፣</u>**

200. የመንግሥት የልማት ፕሮጀክት አስፈፃሚዎች አጥንተው ባቀረቡት እና በፀደቀላቸው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ገንዘብ መጠንና የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራቸው እንዲጠናቀቅ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለተፈፃሚነቱም መመሪያ ሊዘጋጅ ለተጨማሪው ጊዜና ገንዘብ ገደብ (Maximum limit) ሊወሰንለት ይገባል፡፡

**<u>ፕሮጀክቱ አዋጭ መሆኑ/አለመሆኑ ጥናቱ ተጀምሮ ከፍተኛ ወጪ ከተደረገበት በኋላ የተቋረጠ ፕሮጀክት ስለመኖሩ፣</u>**

201. አስፈፃሚ መ/ቤቶች ለሚያዘጋጇቸው የፕሮጀክት ጥናቶች ውጤታማነት ከመነሻ ሐሳብ ጀምሮ፣ መሟላት ስለሚገባው ቅደም ተከተል ለምሳሌ ቢጋር (Terms of

Reference/TOR) የማዘጋጀትን ኃላፊነት በግልፅ እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለተፈፃሚነቱም የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፣ ገለፃ ማድረግና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

<u>የፕሮጀክቶችን ሥራ በሚከታተሉት ሁለቱ ዳይሬክቶሬቶች መካከል ተገቢው ቅንጅታዊ አሰራር ስላለመኖሩ፣</u>

202. የልማት ፕሮጀክቶች አስፈፃሚዎች በቅድመ ትግበራ ግምገማ ወቅት የተሰጣቸውን አስተያየት ተፈፃሚ እንዲያደርጉ፣ የፕሮጀክት ዑደትን ጠብቀው ሥራቸውን እንዲያከናውኑና ብቃት ያለው የፕሮጀክት አስተደደር ሥርዓት እንዲሠፍን ለማድረግ፣ እንዲሁም ወቅታዊ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት በተሟላ መልኩ እንዲቀርብና የተጠያቂነት መርሕ ተግባራዊ እንዲሆን ለማስቻል በልማት ዕቅድና ጥናት እና በበጀት ዝግጅትና አስተዳደር የሥራ ዘርፎች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር እንዲሰፍን መደረግ አለበት፡፡

<u>ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀርበው የሩብ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ለሚኒስትሮች ም/ቤት የሚቀርብ ስላለመሆኑ</u>

203. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም በመከታተልና በማጠናቀር ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ተፈፃሚ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የሪፖርቱ ይዘትም መንግሥት ለሚያደርገው ክትትልና ውሣኔ አሠጣጥ ግብዐት ሊሆን በሚችል መልኩ በፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ያሉ ዋና ዋና ችግሮች የተመለከቱበት ሊሆን ይገባል፡፡

<u>ከአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚቀርበው የፋይናንስ እና የፊዚካል አፈፃፀም ሪፖርት ይዘት ወጥነት የሌለውና በፕሮጀክት ክትትል መመሪያ መሠረት ስላለመሆኑ፣</u>

204. እያንዳንዱ የፕሮጀክት አስፈፃሚ መ/ቤት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያቀርበው የአፈፃፀም ሪፖርት ወጥነት ያለው፣ የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀሙን የሚያመላክት፣ የታቀደ እና የተከናወነውን በንፅፅር የሚያሣይ እንዲሆን መመሪያ ሊተላለፍና ተፈፃሚ እንዲሆን ጥረት መደረግ አለት፡፡

**የፕሮጀክቶች አተገባበር ሂደትን አስመልክቶ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የሚከናወነው የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የተቋረጠ ስለመሆኑ፣**

205. ለእያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት የተለዩትና የሥራ ድርሻቸው በዝርዝር እንዲታወቅ ከተደረገው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በፕሮጀክቱ የክትትልና ግምገማ ሥራ ላይ ተሣታፊ የሚሆኑበት ሥርዓት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

**በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በአስፈፃሚ መ/ቤቶች የሚዘጋጀው መረጃ ተመሳሳይ ስላለመሆኑ፣**

206. እያንዳንዱ የልማት ፕሮጀክት ከመነሻ ጥናት ጀምሮ የፕሮጀክቱ ሥራ እስከ ተጠናቀቀበትና የትግበራ ሥራ እስከ ጀመረበት ጊዜ ያለውን ሂደት (የድህረ ግምገማን ጨምሮ) መረጃ እንዲዘጋጅለት ያስፈልጋል፡፡ መረጃዎቹም በአስፈፃሚ መ/ቤቶችና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት ሊገኙና ተመሣሣይነት ያላቸው እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም እንዲሆን ተገቢው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

**ለልማት ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ በየደረጃው የሚለቀቀው ተጨማሪ ገንዘብ ቀደም ብሎ የተለቀቀው በትክክል በሥራ ላይ መዋሉ ሳይረጋገጥ ስለመሆኑ፣**

207. ለልማት ፕሮጀክቶች ሥራ ማስፈፀሚያ በየደረጃው (Phases) የሚለቀቀው ገንዘብ በትክክል በሥራ ላይ መዋሉ በቅድሚያ የሚረጋገጥበት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡ ለዚህም ተፈፃሚነት የትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት ወጪ ከመፍቀዱ በፊት ቀደም ብሎ የተፈቀደ ገንዘብ በትክክል ለተባለው ሥራ ወጪ ለመሆኑ ማረጋገጫ የሚሆን ሪፖርትና የግምገማ ውጤት እንዲቀርብለት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**ሥራቸው ለተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የድህረ ትግበራ ግምገማ የማይከናወን ስለመሆኑ፣**

208. ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋፅኦ ያላቸው ፕሮጀክቶች በቅድሚያ እየተለዩና የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚያስፈልጋቸው መሆኑም በቅድሚያ እንዲታወቁ በማድረግ፣ እቅድ በማዘጋጀትና ጉዳዮ የሚመለከታቸውን አካላት ተሣታፊ በማድረግ የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወንበት ሥርዓት እንዲዘረጋ መደረግ አለበት፡፡ የግምገማ ውጤቱም ሪፖርት ተዘጋጅቶለት ለውሣኔ ሰጪ አካላት ሊቀርብና በመረጃነትም ሊጠበቅ ይገባል፡፡

209. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለስራችን መቃናትና ትብብር ላደረጉልን በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የልማት እቅድና ጥናት ዳይሬክቶሬት፣ የበጀት ዝግጅትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ የመንግስታት ትብብር ዳይሬክቶሬት፣ የትሬዠሪ ዳይሬክቶሬት እና የመንግስት ፋይናንስ

ዘርፍ ዳይሬክቶሬት፣ የሴክተር አስፈፃሚ መ/ቤቶች የኘላን እና ኘሮግራም ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች፣ ለእንዳቶ-ጋሰራ የመንገድ ሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ መሀንዲስ እንዲሁም ለወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤትና ለሀረሪ ውኃ ሥራዎች ጽ/ቤት ኃላፊዎች ሥስጋና እናቀርባለን፡፡

# **አባሪ**

***የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት***

## ***የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች* (Evaluative Criteria)**

***ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፣*** ***የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር***

| *የኦዲት ትኩረትአ ቅጣጫዎች* *Audit Issues* | ***የኦዲት መስፈርቶች*** */Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| 1. *የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ወጥነት ባለው ሥርዐት የሚዘጋጁ፣ ተገቢው ቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚከናወን፣ የሥራ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት የተዘረጋ እና የርክክብና የድህረ ትግበራ ግምገማ የሚከናወን መሆኑን ማጣራት፣* | |
| 1.1. *የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ ትግበራ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው የፕሮጀክቶች አዘገጃጀት መመሪያ መሠረት ወጥነት ባለው አሠራር ተዘጋጅተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚቀርቡ መሆኑን ማረጋገጥ፣* | *ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚያከናውነው የቅድመ ትግበራ ግምገማም ሆነ የክትትል ስራ የሚያስፈልገው የሰው ሀይል መስፈርት ሊዘጋጅለት፣በመዋቅሩ መሰረት ሊሟላና የስራ ድርሻ መዘርዝር እንዲሁም የዳይሬክቶሬቱ የስራ ሃላፊነትና ተግባር በጽሁፍ ለሚመለከታቸው ሰራተኞች እንዲደርስ መደረግ ይኖርበታል፡፡* |
| | *ለፕሮጀክት ግልጽ የሆነ መመልመያ መስፈርት በሚ/ር መ/ቤቱ መዘጋጀት እና ለአስፈጻሚ መ/ቤቶች እንዲደርስና ለመድረሱም መረጋገጥ አለበት፡፡* |
| | *የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የመንግሥት ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት እና የአፈፃፀም ሥርዐት መመሪያን ለሚመለከታቸው የፕሮጀክት አስፈጻሚዎች ማስራጨት፣የግንዛቤ ማዳበሪያ ስልጠናና፣ ቴክኒካዊ ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡* |
| | *ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት የምልመላ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡ ይህም በሚ/ር መ/ቤቱ መረጋገጥ አለበት፡፡* |
| | *የፕሮጀክት አስፈጻሚዎች በምልመላ ሂደት የተመረጡትን የፕሮጀክት ሃሳቦች የቅድመ አዋጪነት* (pre-feasibility study) *እና የአዋጪነት ጥናት* ( feasibility study) *ማከናወን ይገባቸዋል፡፡* |
| | *በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሊሳተፉ የሚገባቸው አጋር ድርጅቶች በቅድሚያ ተለይተው መታወቅ እና ኃላፊነታቸው በዝርዝር ተለይቶና በጽሁፍ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት፡፡* |
| | *ለቅድመ ትግበራ ምዘና በቀረቡ የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች ላይ የተመለከቱትን ክብደት የሚሰጣቸው ጉዳዮች (ስራዎች) በመለየት ከአጋር ድርጅቶች ጋር ውይይት ሊደረግባቸውና ስምምነት ላይ ሊደረስባቸው ይገባል፡፡የስምምነት ሰነድ መዘጋጀት አለበት፡፡* |
| | *የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ዝርዝር የእቅድ አፈጻጸም መርሃግብር ሊኖረው ይገባል፡፡ በዚህ መርሃ ግብር ላይም የወጪ ግምት፣ የተመደበ ሀብት፣ (የሰው ሀይልና ማቴሪያል) የቁጥጥር ስርዐት እና አዋጪነቱን ሊገልጽ የሚችል ሰነድ፣ ፕሮጀክቱ ሥራ የሚጀምርበትና የሚጠናቀቅበት ቀን መገለጽ አለበት፡፡* |
| | *ፕሮጀክቱ ሊያመጣ የሚችለው ውጤት በቅድሚያ መገምገም እና በፅሑፍ* |

| *የኦዲት ትኩረትአ ቅጣጫዎች*<br>*Audit Issues* | **የኦዲት መስፈርቶች** /*Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| | በሰነዱ ላይ መግለፅ ይኖርበታል፣ |
| | ለከፍተኛ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ግምገማ ጥናት (environmental impact assessment ) መካሄድና በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መፈቀድ አለበት፣ይህም ለቅድመ ትግበራ ግምገማ መቅረብ አለበት፡፡ |
| | ለቅድመ ትግበራ ግምገማ (የፕሮጀክት ምዘና) የሚፈጀው ጊዜ፣የተለያዩ ሴክተሮች አስፈጻሚ አካላት ፕሮጀክቶቻቸውን ለምዘና መቼ ማቅረብ እንዳለባቸው፣በምዘናው ታይተው የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጣቸው በስንት ጊዜ ውስጥ ማስተካከያውን ሰርተው ማቅረብ እንዳለባቸው፣ ወዘተ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለአስፈፃሚዎች በቅድሚያ የሚገለጽበት አሰራር የአፈጻጸም አመላካች ሊኖራቸው ይገባል፡፡ (Performance indicators) |
| 1.2 ለማናቸውም የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ ከመፈቀዱ በፊት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚከናወንባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣ | የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶች ለፋይናንሲንግ ጥያቄ ለገ/ኢ/ል/መ/ቤቶች ከመቅረባቸው በፊት ከሚያስፈጽሟቸው የክፍላተ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ዓላማዎችና ከተለያዩ የፕሮጀክት ገጽታዎች አኳያ የፕሮጀክት ጥናት ሰነዶችን ይዘቶች ትክክለኛነት የማረጋግጥና የፕሮጀክት ዝግጅት አካል የሆነ የሪቪው ሥራ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፣ይህም በቅድሙ ትግበራ ግምገማ ወቅት መረጋገጥ ይኖርበታል፣ |
| | በዝግጅት ሂደት እንዲያልፍ ለተመረጠ ከፍተኛ ፕሮጀክት የቅድመ አዋጪነት ጥናት መካሄድ አለበት፡፡ ይህም በቅድመ ትግበራ ግምገማ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ |
| | በየአመቱ በሚ/ር መ/ቤቱ በበጀት የሚታቀፉ አዳዲስ ፕሮጀክቶች በሚ/ር መ/ቤቱ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሂደት ማለፋቸው መረጋገጥ አለበት፡፡ ለዚህም አገልግሎት ቅድመ ትግበራ ግምገማ ያለፉ ፕሮጀክቶች ተመዝግበውና ተጠናቅረው በመረጃነት የሚጠበቁበት ሥርዓት ሊኖር ይገባል፣ |
| | ማንኛውም የመንግስት የልማት ፕሮጀክት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚከናወነው የቅድሚያ ትግበራ ግምገማ ሂደት ከመፈቀዱ በፊት ወደ ትግበራ መግባት የለበትም፣ |
| | ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት በጀት ከመፈቀዱ በፊት በቅድመ ትግበራ ግምገማ ወቅት እንዲያሟላ የተጠየቀውን (በአስተያየት የተገለፀውን) በቅድሚያ ማሟላቱ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | ለሚ/ር መ/ቤቱ ለቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሰነዶች ወጥ ይዘትና የተሟላ ዝርዝር ጥናት ሊኖራቸው ይገባል፣ ለመሟላቱም የማረጋገጫ ደብዳቤ መዘጋጀት አለበት፣ |
| | በፌደራል መንግስት አስፈጻሚ መ/ቤቶች ደረጃ የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች( ቻነል 2) በሚ/ር መ/ቤቱ የቅድመ ትግበራ ግምገማ ሂደት ሊያልፉ ይገባል፣ |
| | የውጭ እርዳታ ድጋፍ እንዲፈለግላቸው ከብሔራዊና ክልላዊ መንግስታት አስፈጻሚ መ/ቤቶች ለሚ/ር መ/ቤቱ ለቅድመ ትግበራ ግምገማ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በፌደራል የሴክተር አስፈጻሚ መ/ቤቶች በኩል ቀደም ብለው መታወቅና ተቀባይነት ማግኘት አለባቸው፡፡ |
| | የልማት ፕሮጀክቶች ለቅድመ ትግበራ እና ለፋይናንሲንግ ጥያቄ በመመሪያው በተመለከተው የጊዜ ሰሌዳ (በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ (ከሀምሌ/1-መስከረም/30) መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | በቅድመ ትግበራ ምዘና ወቅት የተለያዩና መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች በድጋሜ ለፍተሻ(ምዘና) በሚቀርቡበት ወቅት ከፕሮጀክት ሰነዱ ጋር በማስረጃነትና በአባሪነት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡ |
| 1.3 የግንባታም ሆነ የትግበራ ሥራ በማከናወን ላይ በሚገኙ ማናቸውም የመንግሥት ፕሮጀክቶች ላይ ሚኒስቴር | ሚኒስቴር መ/ቤቱ በልማት ፕሮጀክቶች ላይ ለሚያከናውነው የክትትልና ግምገማ ስራ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | የፕሮጀክት አስፈጻሚዎች በጸደቀው የፕሮጀክት ሰነድ መሰረት ፣በፕሮጀክት |

| *የኦዲት ትኩረትአ ቅጣጫዎች*<br>*Audit Issues* | **የኦዲት መስፈርቶች** /*Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| መ/ቤቱ እንዲሁም አስፈፃሚ መ/ቤቶች የክትትልና ግምገማ ሥራ ቋሚ በሆነ የጊዜ ሠሌዳ መሠረት የሚያከናውኑ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | የድርጊት መርሃ ግብር ፣በቁጥጥርና ክትትል (monitoring & evaluation)መመሪያ (guideline) እንዲሁም በTOR መሠረት በትክክል የፕሮጀክቱን የስራ ሂደት፣ ግብዓት ፣ውጤት፣ ስኬት እንዲሁም የፕሮጀክቱን ፋይዳ (impact) በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካላት ስለ ፕሮጀክቶች የስራ አፈጻጸም በየሶስት ወሩ የክትትልና ግምገማ ውጤት ሪፖርት እየተዘጋጀ ለሚ/ር መ/ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ስለተገኘው የክትትልና የግምገማ ውጤት ሚ/ር መ/ቤቱ በየሩብ ዓመት ወይም በየአመቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሪፖርት ማድረግ አለበት፣ |
| | የፕሮጀክቶች አተገባበር ሂደትን አስመልክቶ ሚ/ር መ/ቤቱ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የግምገማ ስራ ሊያከናውንና ስለውጤቱም ሪፖርት በማዘጋጀት ለበላይ አካል የሚቀርብበት ስርዓት መኖር አለበት፡፡ |
| | በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሚደረገው የፕሮጀክቶች ክትትልና ግምገማ በሪፖርት ላይ ብቻ የተወሰነ መሆን የለበትም፡፡ አልፎ አልፎ ፕሮጀክቱ ባለበት ቦታ ተገኝቶ የሚደረግ ሊሆን ይገባል፣ |
| | ገኢ/ል/ሚር የፋይናንስ ምንጫቸው በውጭ እርዳታ ብድር የሆኑ በፌደራል መንግስትና በክልል መንግስታት በጥምር እንዲሁም በክልል መንግስታት የሚተገበሩትን የልማት ፕሮጀክቶችን የስራ ሂደት በየሩብ ዓመት በሚቀርቡት የሥራ ሪፖርት እንዲሁም አልፎ አልፎ የመስክ ጉብኝት በማድረግ መከታተል ይኖርበታል፣ |
| | በቅድመ ትግበራ ግምገማ (ምዘና) ያለፉ ፕሮጀክቶች ከተፈቀደላቸው ዲዛይንና ዝርዝር ስራዎች ውጪ ለሚጨመሩና ለሚቀነሱ ጉዳዮች በድጋሜ ቀርቦ ካልተፈቀደ በስተቀር መከናወን የለበትም፡፡ ይህም ጉዳይ በክትትልና ግምገማ ወቅት መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | በክትትልና ግምገማ ወቅት የታዩና መስተካከል የሚገባቸው ስራዎች ለፕሮጀክት አስፈጻሚው አካል በሪፖርት የሚገለጽለት፣አስፈጻሚውም ለማከናወኑ ሪፖርት የሚያቀርብበትና በትክክል ለመከናወኑም ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| 1.4 ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት በየደረጃው (Phases) ለሥራ ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ ከመፈቀዱ በፊት የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ተዘጋጅቶና ቀደምት ሥራዎች በትክክል ለመከናወናቸው የሚረጋገጥ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | አስፈጻሚዎች በተዘጋጀው የሪፖርት ፎርማት ፣በመመሪያው እና TOR በተመለከተው መሰረት በፕሮጀክት ዝግጅት፣ በፕሮጀክት ትግበራ እና በፕሮጀክት ኦፕሬሽን ፕሮሰስ (project operation process)ዝርዝር መረጃዎችን በመሰብሰብ የተሟላ ፣የተደራጀና ግልጽ የሆነ የስራ ክንውን ሪፖርት (progress report) ማዘጋጀት እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ |
| | በምዘና ያለፉ ፕሮጀክቶች በየደረጃው የስራ ማስፈጸሚያ በጀት ከመለቀቁ በፊት ማሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ዝርዝር መስፈርቶችና ግዴታዎች ሊዘጋጁ፣ለአስፈጻሚ አካላትም በጽሁፍ ሊደርሱ ይገባል፡፡ |
| | የፕሮጀክቶች አስፈጻሚ አካላት በየደረጃው እንዲለቀቅላቸው ለሚጠይቁት ገንዘብ በቅድሚያ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት(የፊስካልና የፋይናንስ) እንዲያዘጋጁ መደረግ አለበት፡፡ |
| | ገ/ኢ/ል/ሚ/ር የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ ገንዘብ በየደረጃው (phases) ከማጽደቁ በፊት የክትትልና ግምገማ ስራ(የመስክ ስራን ጨምሮ) በማከናወን ሪፖርት ማዘጋጀትና ለቀጣይ ስራ ገንዘብ እንዲለቀቅ በጽሁፍ ለበጀት ዝግጅት ዳይሬክቶሬት ማሳወቅ አለበት፡፡ |
| 1.5 የልማት ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እና ገንዘብ እንዲሁም በተገቢው መንገድ ለመጠናቀቃቸው የግምገማ ሥራ የሚከናወን እና ርክክብ የሚፈጸም | • ማንኛውም የመንግስት የልማት ፕሮጀክት<br>• በታቀደው ጊዜ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡<br>• በታቀደለት ወጪ መጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡<br>• የተጠናቀቁና ርክክብ የሚፈጸምባቸው ፕሮጀክቶች ግምገማ ተከናውኖ ሪፖርት መዘጋጀት አለበት፡፡<br>• በተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ርክክብና ግምገማ ላይ አጋር ደርጅቶች |

| *የኦዲት ትኩረትአ ቅጣጫዎች*<br>*Audit Issues* | **የኦዲት መስፈርቶች** /*Evaluative Criteria/* |
|---|---|
| *መሆኑን ማረጋገጥ፣* | *መሳተፍ ይኖርባቸዋል።* |
| | የፕሮጀክቱ ስራ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት በጀመሩ ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ መደረግ ይኖርበታል፡ |
| | የልማት ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ሲገቡ የተሟላና ወጥ የሆነ የክትትልና የቁጥጥር ድጋፍ በማድረግ በአፈጻጸም ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችን ፈጥኖ ለመቅረፍ የሚያስችሉ የመፍትሔ አማራጮች የሚቀርቡበት ሥርዓት መዘርጋት አለበት።በሥርዓቱም አመርቂ ወጤት የሚያስመዘግቡ የፕሮጀክት ባለሙያዎችና የአመራር አካላት የሚበረታቱበት ፕሮጀክቱ ተገቢ ትኩረትና ድጋፍ ባለማግኘቱ የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ ባይችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች እና የአመራር አካላት ተጠያቂ የሚሆኑበት አሰራር ሊኖር ይገባል፣ |
| | ግንባታ የጀመረ ፕሮጀክት በገንዘብ /ፈንድ/ እጥረት ምክንያት እንዲቋረጥ መደረግ የለበትም፣ |
| | ከፍተኛ የኢኮኖሚና ማህበራዊ አስተዋጽኦ አላቸው ተብሎ በተለዩት ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ የድህረ ትግበራ ግምገማ (ፕሮጀክቱ ወደ አገልግሎት ከገባ ከተወሰኑ ዓመታት በኃላ ቀደም ብለው በተቀመጡ የፕሮጀክቱ ዓላማዎች መሠረት የተገኙ የግብ ስኬቶችን እና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦችን) ሊካሄድ ይገባል። ለድህረ ትግበራ ግምገማ ማከናወኛም የጊዜ ገደብ በመስፈርትነት ሊዘጋጅለት ይገባል። |
| | በሥራው ሂደት የተገኙ ጥሩ ተሞክሮዎች ለሌሎች ኘሮጀክቶች እንዲተላለፉ ችግሮች ደግሞ እንዳይደገሙ መረጃዎች ሊያዙ ይገባል፣ |